አምስቱ አዕማደ ምሥጢር

መግቢያ

አምስቱ አዕማደ ምሥጢር የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ምሥጢረ ሥላሴ
2. ምሥጢረ ሥጋዌ
3. ምሥጢረ ጥምቀት
4. ምሥጢረ ቁርባን
5. ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ፷ቱ አዕማደ ምሥጢራትን በተመለከተ *"ከሁላችሁ ይልቅ በልሳኖች እናገራለሁ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ ነገር ግን ሌሎችን ደግሞ አሰተምር ዘንድ በማኅበር አልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ"* *1ቆሮ 14÷18-19* አለ። አምስት ቃላት ያለው አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት እንደሆኑ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ያስረዳሉ።

አዕማድ

አዕማድ አምድ ከሚለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን ሲበዛ አዕማድ ይባላል። ትርጉሙ በሁለት መንገድ ይፈታል።

1. ለቤት ሲሆን ምሰሶ ማለት ነው። ምሰሶ ቤትን ተሸክሞ እንደሚያጸናው ሁሉ እነዚህም ምሥጢራት አንድን ክርስቲያን በክህደት በጥርጥር እንዳይወድቅ አጽንተው ይደግፉታል።
2. ዐምድ ለጽሕፈት ሲሆን ደግሞ ለገጽ ስፋት መከፈያነት ያገለግላል። ለንባብ መመጠኛ ነው። እንዲሁ ባሕርየ ሥላሴን ከመጠን አልፈን እንዳንመረምር የሚገድብ በመሆኑ የተሰጠ ስያሜ ነው።- *ሮሜ 12÷13*

Scanned by CamScanner

ምሥጢር

አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት የምሥጢር ትምህርቶች ናቸው። ምክንያቱም በሥጋዊ ጥበብ መመርመርና መረዳት የማይቻል ስለሆነ ነው። ምሥጢራቱን ለመረዳት ትሕትና ጸሎትና ትምህርት አስፈላጊ ነገሮች ናቸው። አንዳንዶች ግን ምሥጢራት ሲባል ትምህርቶቹ እውነት ስላልሆኑ ለማድበስበስና ከተጠያቂነት ለማምለጥ ይመስላቸዋል። ቤተ-ክርስቲያን ግን እነዚህንና መሰል ትምህርቶች ምሥጢራት ብላ ስትጠራ ትምህርቶቹ በሥጋዊ ምርመራ የማንደርስባቸው ስለሆነና በመንፈሳዊ ምርመራ እንኳ ሐዋርያው *"ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ" ፩ቆሮ13÷12* እንዳለ እውቀታችን የተወሰነ እና ገደብ ያለው በመሆኑ ነው።

አንዳንዶች መንፈሳዊ ምሥጢራትን በሙላት እንደአወቁ ሆኖ ይሰማቸዋል። ሌሎች ደግሞ በሥጋዊ ምርመራ ሊያውቁት እንደሚችሉ ሆኖ ይሰማቸዋል። ነገር ግን ብዙው ነገር ምሥጢር ነው።

ቅዱስ አትናቴዎስ በ358 ዓ.ም ለመነኮሳት በጻፈው ደብዳቤ ስለ ሥላሴ ምሥጢርነት ገልጾ ነበር። አትናቴዎስ ሲናገር ስለ እግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት መረዳት *(ማወቅ)* የልብሱን ጠርዝ *(ጫፍ)* ብቻ እንደማወቅ ነው ብሎ ነበር። የቀረው በኪሩቤል ከንፍ ተሸፍኗል። የበለጠ በመረመርኩ ቁጥር የበለጠው ምሥጢር ሆኖ ይቀራል በማለት ተናግሮአል።[29] በአንከሮም ሆኖ ከመዝሙረኛው ጋር *"እውቀትህ ከእኔ ይልቅ ተደነቀች፤ በረታች፣ ወደ አርሷም ለመድረስ አልችልም"* ሲል መስከረ *መዝ 138÷6*። ማን የእግዚአብሔርን ሐሳብ *(ምሥጢር)* በሙላት ሊያውቅ ይችላል?

መጽሐፍ ቅዱስ ከአምስቱ አዕማደ ምሥጢራት ውስጥ የተወሰኑትን ምሥጢራት ብሎ ሲጠራቸው እናገኛለን። ለምሳሌ ምሥጢረ ሥጋዌን በተመለከተ *"ከዘመናት በፊት ለክብራችን የወሰነውን ተሰውሮም የነበረውን የእግዚአብሔር ጥበብ በምሥጢር እንናገራለን" ፩ቆሮ2÷7* ይላል ሮሜ *16÷25፣ ቆላ ፩÷16፣ ኤፌ፩÷9* ተመልከት።

29. History of Christian Church vol III p 138.

Scanned by CamScanner

ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታንን በተመለከተ ደግሞ "እነሆ አንድ ምሥጢር አነግራችኋለሁ ሁላችን አናንቀላፋም" ይላል 1ቆሮ15÷51:: በዚህ መሠረት ምሥጢራቱን በዝርዝር ወደ መመልከት እንሄዳለን::

Scanned by CamScanner

ምሥጢረ ሥላሴ

"በሦስት የተገመደ ገመድ ፈጥኖ አይበጠስም" መክ 4÷12

ቅዱስ ቄርሎስ ከአምስቱ አዕማደ ምሥጢር መጀመሪያ መማር ያለብን ምሥጢረ ሥላሴ መሆኑን ሲያስረዳ *"መቅድመ ኩሉ ንሰብክ ሥላሴ ዕራዩ"* ትርጉሙ ከሁሉ አስቀድመን የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት እናሰተምራለን ብሎአል::ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ አድርገን ምሥጢረ ሥላሴን እንመልከት::

የሥላሴ መጠሪያዎች

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሥላሴ ከሚለው ስም ጀምሮ ልዩ ልዩ በሆኑ መጠሪያዎች በመጠቀም ስለ ሥላሴ ታስተምራለች:: በዚህ ክፍል የተወሰኑትን የሥላሴ መጠሪያዎች እንመልከት::

ሥላሴ:-ሥላሴ ሠለሰ ካለው የግእዝ ግስ የወጣ ሲሆን ሦስትነት ማለት ነው:: ቃሉን ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሙበት ጠርጠሉስና (Tertullia) ቴዎፍሎስ ዘአንጾኪያ (Teophilos of Antioch) እንደሆኑ ይነገራል::

ሥላሴ የሚለው ቃል በወንጌል

የአንድነትና የሦስትነት ተቃዋሚዎች ለከህደታቸው እንደማስረጃ አድርገው ሥላሴ የሚል ቃል በአንድም ቦታ በወንጌል አልሰፈረም ይላሉ:: አቡነ ሺኖዳ ለዚህ ምላሽ ሲሰጡ አባቶቻችን ሐዋርያት ከርስትናን የሰበኩት በብዙ አማልክት *(polytheism)* በሚያምኑ አረማውያን በሆነ ሃገራት መካከል በመሆኑ ሥላሴ *Trinity* ወይም ሦስት *Three* የሚለውን ቃል አልተጠቀሙም ብለዋል:: ሆኖም ግን ከሐዋርያት ሁሉ ረጅም ዕድሜ የኖረው ቃሉን *(ሦስት)* የሚለውን ተጠቅሞበታል ብለዋል[30]::- *ዮሐ 5÷7*

30. Jehovah witnesses and their Heresies.p 33.

Scanned by CamScanner

ሥላሴ ዋሕድ፦- ሌላው የሥላሴ መጠሪያ ሥላሴ ዋሕድ የሚለው ነው። ቃሉ የሚያመለክተን በአንድ አግዚአብሔርነት ከሚገኝ ከሦስቱ አካላት በቀር መንትያ ወይም ተመሳሳይ የሌለውና ብቻውን የሚኖር ሦስት፤ "ሦስትነትን" የሚያሳይ መጠሪያ ነው።

ሥላሴ ዘላለም (ዘላለም ሥላሴ)፦- ይህ መጠሪያ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የሚል የሥላሴ መጠሪያ ስም *(አቃኒም)* ከጊዜ በኋላ የተገኘ ሳይሆን ከዘላለም በሥላሴነቱ የነበረ መሆኑን የሚገልጽ መጠሪያ ነው።

ሥሉስ ቅዱስ (ቅዱሰ ሥሉሰ)፦- ሦስትነት ያለው አንድነትን የሚያመላክት መጠሪያ ነው።ሥሉስ ብሎ በብዙ ሦስትነትን፣ቅዱስ ብሎ በነጠላ አንድነትን ያመለክታል።

ቅድስት ሥላሴ፦- ትርጉሙ የተቀደሰች ሦስትነት ማለት ሲሆን ቅድስት ሲባል ለሦስትነት የተቀጸለ ወይም የተነገረ ነው።_

ልዩ ሦስትነት፦- ምንም እንኳ ለሦስትነትና ለአንድነት ምሳሌ የሚሆኑ ነገሮች ቢኖሩም፣ምሳሌዎቹ የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት ጠንቅቀው የሚያስረዱ ባለመሆናቸው በሌላ አባባል ምሳሌ ዘየሐፅፅ ስለሆኑ የሥላሴ ነገር ከሁሉ ልዩ ነው ለማለት ልዩ ሦስትነት ተብሏል።

ይህ እንግዲህ ከሆነ አንድነትንና ሦስትነትን ለመረዳት የአባ ሕርያቆስን ምክር መከተል ዐቢይ ጉዳይ ነው። ምክንያቱም አንድነትና ሦስትነትን መረዳት የሚሻ ሰው ሥላሴ የማይለያዩበትንና የማይቀላቀሉበትን ባሕርይ ለይቶ ማወቅ ያለበት በመሆኑ ነው።

ሕርያቆስ ሲያስጠነቅቅ፦- *"ከመ፧ ነአምን፡ ወከመ፧ ንትአመን፡ ድማሬ፡ ወጉባሬ፡ እንዘ፡ ኢንፈልጥ፡ ወኢንሌሊ፣ ከመ ኢይኩን፡ ብዑደ ወኢፍለጠ"* (ቅዳሴ ማርያም) በማለት መለያየት የሌለብንን እንዳንለያይ አስጠንቅቋል።

ትርጉሙ አንድነት ከሦስትነት ፈጽሞ እንዳይለይ፡ አንድነት ከሦስትነት በባሕርይ ሳንለይ ሦስትነትን እናምናለን። ሦስትነት ከአንድነት በባሕርይ ፈጽሞ እንዳይለይ፡ ሦስትነትን ካንድ ባሕርይ ሳንለይ አንድነትን እናምናለን ማለት ነው።

Scanned by CamScanner

እነጋገሩ የሚያስረዳው በእንድኑ ሦስትነት፣ በሦስትኑ ደግሞ እንድነት ያለ በመሆኑ ሳንለያይ ማመን ተገቢና ወላኝ መሆኑን ነው::ምክንያቱም እንድ ሰው እንድኑን ሊያስብ ሦስትኑን ትቶ ወይም ደግሞ ሦስትኑን ሊያስብ እንድኑን አስቀርቶ ከሆነ ምሥጢረ ሥላሴን ለመረዳት አይቻለውም::

መቃላቅል ወይም እንድ አድርገን መመልከት የሌለብን ቀላቅሎ ወይም እንድ አድርጉ ከመመልከት መቆጠብ እንደሚገባ ሊመከር ደግሞ " *ንፍለጥ ወንሌሊ ከመ ኢይኩን ሕውከ*" አለ:: ማለት እንድነትን ከሦስትነት ሦስትነትን ከእንድነት ጋር በእካል የተቃላቀለ እንዳይሆን፣ እንድነትን ከሦስትነት: ሦስትነትን ከእንድነት በእካል እንለይ ማለት ነው:: ለምሳሌ እንድ ሰው ሦስቱን የሥላሴ እካላት ከእንድነት ጋር ቀላቅሎ እንድ ነው ብሎ ቢያስብ መቃላቀል ወይም እንድ አድርጉ መመልከት የሌለበትን ነገር ቀላቅሎ እየተመለከተ ነው ማለት ነው:: ይህ ደግሞ ስሕተት ነው::

ስለዚህ ምሥጢረ ሥላሴን ለመረዳት ከላይ የተገለጠውን የአባ ሕርያቆስ ማስጠንቀቂያ መከተል ቁልፍ ነገር ነው ማለት ነው:: ምክንያቱም እግዚአብሔር እንድ ነው ሲባል ሦስትነት የሌለው ማለት አይደለምና:: ሦስትነት አለው ሲባልም እንድነቱን በማስቀረት አይደለም:: ይህን መነሻ በመያዝ ምሥጢረ ሥላሴን መማር እጅግ ጠቃሚ በመሆኑ ሦስትንና እንድነትን በዝርዝር እንመልከት::

ሦስትነት

ሦስትነት ሲባል ሦስት ማለት አይደለም::ሦስት ስንል የሚያመለክተው እንድነት የሌለውን ሦስት የተለያዩ ነገሮችን ነው:: ሦስትነት ስንል ግን እንድነት ላለው እካል መናገራችን ነው:: በምሳሌ ለማየት ፀሐይ እንድ ናት ነገር ግን ሦስትነት *(ከበብ፣ ብርሃን፣ ሙቃት)* አላት:: ስለዚህ ፀሐይ ሦስትነት አላት እንጂ ሦስት አይደለችም:: በዚህ መሠረት የሥላሴም ሦስትነት በእንድ እግዚአብሔርነት ውስጥ የሚገኝ መሆኑን እያሰብን እንዝለቅ:: የሥላሴ ሦስትነት በስም፣ በእካላት ግብር፣ በእካል፣ በገጽ እና በኩነት የሚገለጥ ነው:: እነዚህ በዝርዝር ሲታዩ:-

Scanned by CamScanner

በሰም

- አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ (ማቴ 28÷19)
- ልብ፡ ቃል፡ እስትንፋስ (መዝ 32(33)6-11)
- ወላዲ አሥራጺ፡ ተወላዲ፡ ሠራጺ (መዝ 2÷7)፣ (መዝ109(110) ÷3)

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ሰሞች ከጊዜ በኋላ የተሰየሙ ሰሞች ሳይሆኑ አካላተ ሥላሴ በነበሩበት ዘመን ሁሉ የሚጠሩበት ሰም ነው። ሰለሆነም "ኢቃኒም" ተብለውም ይጠራሉ። ኢቃኒም ማለት በመልክና በገጽ ፍጹማን ሆነው ጸንተው የሚኖሩ አካላት ማለት ነው። ሦስቱን አካላት ከሦስቱ ሰሞች መነጠል የማይቻልና ሦስቱ አካላት በነበሩበት ዘመን ሁሉ ሰሞቹ እንደ ነበሩ የሚያሳይ አነጋገር ነው። ዘላለማዊ ሰሞች ናቸው።

- አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ የአካላት ሰም ናቸው።
- ልብ፡ ቃል፡ እስትንፋስ የአኗኗት ሰም ናቸው።
- ወላዲ አሥራጺ፡ ተወላዲ፡ ሠራጺ የአካላት ግብር ሰም ናቸው።

በዝርዝር ለመመልከት ያህል አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የተባሉት ሰሞች የሥላሴ አካላት መጠሪያ ሰሞች ናቸው። መፋለስ ወይም መቀላቀል የለባቸውም። አብ ሁልጊዜ አብ እንጂ ወልድ ወይም መንፈስ ቅዱስ አይባልም። ወልድ ሁልጊዜ ወልድ እንጂ አብ መንፈስ ቅዱስ አይባልም። መንፈስ ቅዱስ ሁል ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንጂ አብ ወይም ወልድ አይባልም። ይህን ነው የሰም መደባለቅ ወይም መፋለስ የለም ያሰኘው።

ሦስቱ ሰሞች ያለመቀዳደምና ያለመከታተል አካላተ ሥላሴ በነበሩበት ዘመን ሁሉ (ለዘላለም) የነበሩ ሰሞች ናቸው። በሰሞቹ መካከል የዓይን ጥቅሻ፣ የከንፈር ንክሻ ስንኳ ያህል መቀዳደም የለባቸውም።

Scanned by CamScanner

አብ ማለት አባት ማለት ሲሆን አባትነቱ ለወልድ ብቻ ነው:: ወልድ ማለት ልጅ ማለት ሲሆን ልጅነቱ ለአብ ብቻ ነው:: መንፈስ ቅዱስ አባትም ልጅም ባለመሆኑ ልዩ ያደርገዋል:: የስም መገናዘብ *(መዋሐድ ወይም አንድነት)* በሦስቱ አካላት ላይ የለም:: ለዚህ ነው በስም ሦስትነት አለ ወይም ልዩ ናቸው የተባለው::

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የተባሉት ስሞች በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ሰፍረው ይገኛሉ:: *"በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም...."ማቴ 28÷19*:: በራእይም *"ስሙና የአባቱ ስም" ራእ14÷1* ተብሎ ተጠቅሶአል:: በአሪት *"ስሙ ማን የልጁስ ስም ማነው?" ምሳሌ 30÷4፣ መዝ 2÷7፣ ዮሐ16÷27-28* ተብሎ ተገልጿል::

የስም ቅደም ተከተል

በቅድስት ሥላሴ መካከል የደረጃ ወይም የመዓርግ ልዩነት የለም *(ሮሜ 11÷36)* በቅዱሳት መጻሕፍት ብዙውን ጊዜ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ተብሎ ተከታትሎ የመቀመጡ ምክንያት ድኅነታችንና ፍጥረታችን በአብ የተወጠነ በወልድ የተከወነ በመንፈስ ቅዱስ የተፈጸመ በመሆኑ ነው:: ይህም ቢሆን ቅሉ ሦስቱ ስሞች እየተቀዳደሙ ተጽፈው ይገኛሉ ::

- የአብ ስም ሲቀድም :- አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ *(ማቴ 28÷19)*
- የወልድ ስም ሲቀድም :- ወልድ አብ መንፈስ ቅዱስ *(2ኛ ቆሮ 13÷13)*
- የመንፈስ ቅዱስ ስም ሲቀድም :- መንፈስ ቅዱስ ወልድ አብ *(1ኛ ቆሮ 12÷4-6)*

በአካላት ግብር ስም

የሥላሴ አካላት በግብር ስም ሦስትነት አላቸው:: የግብር ስም የሚባሉት ወላዲነት አሥራጺነት፣ ተወላዲነትና ሠራጺነት ናቸው:: የአብ የአካሉ ግብር (ሥራ) ወልድን መውለድ መንፈስ ቅዱስን ማሥረጽ ነው:: ወልድ የአካሉ ግብር (ሥራ) ከአብ ብቻ መወለድ ነው:: መንፈስ ቅዱስ የአካሉ ግብር (ሥራ) ከአብ ብቻ መሥረጽ *(መውጣት)* ነው::

Scanned by CamScanner

በመሆኑም አብ ወላዲ አሥራጺ ሲባል፤ ወልድን ይወልዳል መንፈስ ቅዱስን ያሠርጻል:: ወልድ ተወላዲ ሲባል ከአብ ብቻ ይወለዳል:: መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ ሲባል ከአብ ብቻ ይሠርጻል::

ከላይ የተጠቀሱትን ወለደ፣ አሠረጸ ፣ ተወለደ እና ሠረጸ የሚሉትን ቃላት በዕለት ተዕለት በምንጠቀምበት የቋንቋ አገባብ የምንረዳው ከሆነ ለስሕተት መዳረጋችን የማይቀር ነው::በአጠቃላይ በትምህርተ-መለኮት ውስጥ የምናገኛቸውን ቃላት በትክክለኛ ትርጓሜያቸው መረዳት የግድ አስፈላጊ ነገር ነው::ቃላቱ እንዴት እንደሚሠራባቸው ወደፊት በቦታቸው የምንመለከተው ይሆናል::

የአወጣጥ ወይም የጸአት ሁኔታ

መጽሐፍ ቅዱስ የአብን ወላዲነትና አሥራጺነት፣ የወልድን ተወላዲነት፣ የመንፈስ ቅዱስን ሠራጺነት በግልጽ አስፍሮት ይገኛል:: የገለጸውም *"ፀአት* ወይም ***መውጣት***" በሚለው ተመሳሳይ ቃል ነው:: ለምሳሌ ስለ አብ ወላዲነትና ስለ ወልድ ተወላዲነት *(አወጣጥ)* ሲናገር *"ከአብ ወጥቼ ወደ ዓለም መጥቻለሁ" ዮሐ 16÷28* ሲል: ስለ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺነትና ስለ አብ አሥራጺነት ደግሞ *"ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ" ዮሐ 15÷26* በሚል ተመሳሳይ ቃል ሰፍሮ እናገኛለን::

መጽሐፍ ቅዱስ መውጣት በሚል ተመሳሳይ ቃል ያስቀመጠውን የወልድና የመንፈስ ቅዱስን ከአብ መውጣት፤ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ልዩነቱን በሚያሳውቅ ልዩ ልዩ ቃል አስቀምጠውታል:: ይኸውም የወልድን ከአብ መውጣት *"**ተወላዲነት**"* ሲሉት የመንፈስ ቅዱስን ከአብ መውጣት *"**ሠራጺነት**"* በሚል ገልጸውታል:: ተወላዲነት እና ሠራጺነት በሚሉ ሁለት ቃላት መሰየም ያስፈለገው በሁለቱ መካከል ሰፊ የምሥጢር ልዩነት ያለ በመሆኑ ነው:: የአወጣጣቸውም አንድነትና ልዩነት እንደሚከተለው ነው::

Scanned by CamScanner

አንድነቱ፡- አንድነቱ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሁለቱም ከአብ በመውጣታቸው በአንድ ዓይነት ቃል ጸአት *(መውጣት)* በሚል በመገለጹ ነው::

ልዩነቱ፡- ደግሞ የአወጣጣቸው ሁኔታ ነው:: ይኸውም ወልድ ከአብ የወጣው በተወላዲነት *(በልጅነት)* ሲሆን የመንፈስ ቅዱስ ደግሞ በሠራጺነት *(በአሰትንፋሰነት)* በመሆኑ ነው:: ወልድ ተወላዲ እንጂ ሠራጺ አይባልም:: መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ እንጂ ተወላዲ አይባልም - ይህ ልዩነት ነው::

ተወለደ(ተገኘ)ሲባል እንዴት ነው?

ወልድ ከአብ ተወለደ ወይም ተገኘ ሲባል በጥሬው ከተረዳነው መናፍቃን ከወደቁበት የስሕተት ጉድጓድ መውደቃችን የማይቀር ነው:: ጳውሎስ ሳምሳጢ የተባለ መናፍቅ ተወለደ ሲባል በፍጡራን ልማድ *(በአባትና በልጅ)* እንዳለው ዓይነት ነው ብሎ ነበር:: ርዕሰ-መናፍቅ አርዮስም ተወለደ የሚለውን ተፈጠረ በሚል ተርጉሞ ለስሕተት ተዳርጓ ነበር:: ታዲያ ተወለደ ማለት ምን ማለት ነው?

ቤተ ክርስቲያን ወልድ ከአብ ተወለደ ወይም ተገኘ ስትል አብን አከሎ አብን መስሎ፣ ባለመቀዳደም፣ ባለመከፋፈል እና ባለመለያየት ከባሕርይው ተገኘ *(ተወለደ)* ማለቷ ነው:: ተወለደ ሲባል በመልከ ይመስለዋል፣ በክብር ይተካከለዋል ማለት ነው:: ስለዚህ ተወለደ ተብሎ ሲነገር ሁለት ቁም ነገሮችን ማስታወስ ይገባል:: አንደኛው በመለኮቱ መከፈልና መለየት *(ተከፍሎ ተመትሮ)* ሳይኖርበት ነው:: ሁለተኛ በአካሉ ቅደም ተከተል ሳይኖርበት ነው:: ያለመከፈል፣ ያለመለየትና ያለመቀዳደም መወለዱ እንዴት እንደሆነ ሊቃውንት በምሳሌ የገለጡትን እነሆ!

ልደቱ በምሳሌ

አብ ወላዲ ወልድ ተወላዲ ነው ሲባል በሰው ሰውኛ እንዳለው አባትና ልጅ አድርጓ መረዳት አግባብ አይደለም ታላቅ ስሕተትም ነው:: ምክንያቱም በአባትና ልጅ መካከል መቀዳደም፣ መበላለጥ፣ መካፈልና መለያየት አለ:: በአብና በወልድ መካከል ግን

Scanned by CamScanner

እንዲህ ስላልሆነ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የወላዲነትንና የተወላዲነትን ምሥጢር እንረዳ ዘንድ በልዩ ልዩ ምሳሌያት አስተምረዋል::

ከምንጭ እንደ ሚፈልቅ ወንዝ

ቅዱስ አትናቴዎስ የወልድን ከአብ መውጣት ወይም መወለድ በምንጭና በወንዝ መስሎ ተናግሯል:: አትናቴዎስ ሲናገር ወንዝ ከምንጭ እንደሚገኝና ሁለቱ የተለያዩ እንዳልሆኑ ነገር ግን ሁለቱ ሁለት ስሞች ያላቸውና ሁለት የሚታዩ ነገሮች እንደሆኑ ሁሉ፣ አባት ልጅ አይደለም ልጅም አባት አይደለም:: አባት የልጁ *(የወልድ)* አባት ብቻ ነው:: ልጁም የአባቱ *(የአብ)* ልጅ ብቻ ነው አለ::

በተመሳሳይ ሁኔታ ምንጭ ወንዝ ተብሎ እንደማይጠራ፣ ወንዝም ምንጭ ተብሎ እንደማይጠራ ሁሉ፣ ነገር ግን ሁለቱም በቱቦ አማካኝነት ከምንጭ ወደ ወንዝ እንደሚያልፍ ሆኖም አንድ ዓይነት እንደሆነ ውኃ፣ የአብ ባሕርይም *(አምላክነቱ ዘላለማዊነቱ ወዘተ...)* ወደ ወልድ ያለመከፈልና ያለመለየት ወጥቶአል::ይኸውም ጌታ *"ከአብ ወጥቼ ወደ ዓለም መጥቻለሁ" ዮሐ 16÷28* በማለት እንደተናገረው ነው በማለት ተናግሮአል::[31]

ሠለስቱ ምዕት ደግሞ *"ብርሃን ዘእምብርሃን"* በማለት የወልድን ከአብ መገኘት *(መወለድ)* ከፀሐይ በሚወጣ ብርሃን መስለው ተናግረዋል:: መጽሐፍ ጌታን *"እውነተኛ ብርሃን" ዮሐ 1÷9* ይለዋል:: ብርሃን ከፀሐይ ሲወጣ ያለመለየት ያለመከፈል እና ያለመቀዳደም ፀሐይን መስሎ በባሕርይ ተካከሉ እንደሆነ ሁሉ የወልድም ከአብ መወለድ እንዲሁ ነው:: ለዚህ ነው ብርሃን ዘእምብርሃን ከብርሃን የተገኘ ብርሃን የተባለው::- ዕብ 1÷3

በሌላ በኩል ወልድ ተወለደ ሲባል ያልተፈጠረ መሆኑን ያመለክታል:: ምክንያቱም ሰው የሚወልደውን አይፈጥረውምና ነው:: **ዘተወልደ ወአኮ ዘተገብረ** የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ የተባለበት ምክንያት ይኸው ነው::

---

31. The Real Holy Grail.p 108.

Scanned by CamScanner

ተወላዲነት በመጽሐፍ ቅዱስ

አንዳንዶች ሰዎችና መላእክት የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው እንደ ተጠሩ ሁሉ ወልድም የእግዚአብሐር ልጅ መባሉ ተመሳሳይ ነው በማለት በተወላዲነቱ ከአብ ጋር በክብር እንደሚተካከል በመልከ እንደሚመስለው ይክዳሉ::

ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ወልድ *"ልጅ"* የተባለበት መንገድ የባሕርይ እንደሆነና ከፍጡራን የጸጋ ልጅነት የተለየ እንደሆነ ያስረዳናል::

ሐዋርያት ጌታን ***"አንድ ልጅ"*** በሚል በተደጋጋሚ ገልጸውታል::*ዮሐ 1÷18፣3÷18፣1ዮሐ.መ 4÷9፣ 1ዮሐ.መ 1÷14::* ይህ አንድ ልጅ ወይም አንድያ ልጅ የሚለው አገላለጽ ጌታ ከፍጡራን በተለየ በመልከ እንደሚመስለው በክብር እንደሚተካከለውና የባሕርይ ልደት መሆኑን ያሳየናል:: ይህም ***"ብሉጥ ልደት"*** ይባላል:: በዚህ መልኩ የተወለደ ሌላ የለምና የወልድ ልደት ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው ብቸኛ በመሆኑ የተሰጠ ስያሜ ነው::

ቅዱስ ማርቆስም *"የሚወደው አንድ ልጅ ገና ነበረ"* ማር *12÷6* በማለት ልደቱን ተናግሯል:: በዚህም አንድ በማለቱ ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው የባሕርይ ልጅ እንደሆነ ሲገልጥ፣ ያለመቀዳደማቸውን ደግሞ ያለ ልጅ አብ ወይም አባት ተብሎ እንደማይጠራ ጥቅሱ ያስገነዝባል:: አብ የሚለው ስም በኋላ ወልድን በመውለዱ የወጣ እንዳልሆነ አይተናል:: ወልድም ሲባል እንዲሁ ዘላለማዊ ስም መሆኑን ልብ ይሏል::*ዮሐ ፫÷19፣14÷9:: "ነበረው"* የሚለው ቃል ዘላለማዊነቱን ያሳያል::- *ዮሐ 1÷3*

በሌላ በኩል በመጽሐፍ ወልድ *"የአግዚአብሔር ልጅ"* ተብሎ የተገለጸው ከፍጡራን በተለየ ወልድን ብቻ የሚያመለክት አነጋገር ሆኖ ይገኛል::ጌታ ዓይኑን ያበራለትን *(የፈጠረለት)* ዓይነ ስውር በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህ? ብሎ ጠይቆት ነበር:: ዓይነ ስውሩ መልሶ አምን ዘንድ ማን ነው? በማለት በጠየቀ ጊዜ ጌታ "አይተኸዋል ከአንተ ጋርም የሚነጋገረው እርሱ ነው" በማለት በተለየ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ እንደሚታወቅ ገልጾልናል::- *ዮሐ 9÷35-41*

Scanned by CamScanner

ሐዋርያትም ይህን ያውቁ ስለነበር *"ልጁ ያለው ሕይወት አለው፣ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም"* ብለው ጽፈዋል::- *2ዮሐ 5÷12*

የጌታ ልጅነት የባሕርይ ባይሆንና ከፍጡራን የተለየ ባይሆን ኖሮ ቅዱስ ጴጥሮስ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ በማለቱ ለምን አስደናቂ መልስ እንደ መለሰ ተቆጠረ? ለምንስ የአባቴ መንፈስ እንጂ ሥጋና ደም አልገለጠልህም ተባለ? ነገር ግን ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታን *"የእግዚአብሐር ልጅ"* በማለቱ ዓለት ተባለ ይኸውም በተወላዲነቱ በማመኑን ነው::- *ማቴ 16÷13-18*

ዲያብሎስ እንኳን የጌታ ልጅነት ከፍጡራን ልጅነት የተለየ መሆኑን አውቆ ነበር:: *"የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ፣ እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል አለው"* እና *"የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ ከመስቀል ውረድ"* ያለውና ያስባለው የባሕርይ ልጅ መሆኑን ስለተረዳ ነው *ማቴ 4÷3፣ ማቴ 27÷40::* ስለዚህ እነዚህ ሁሉ ጥቅሶች የሚያስረዱት የወልድ ልጅነት ከፍጡራን የተለየ መሆኑን፣ እርሱን ብቻ የሚያመለክት መጠሪያ መሆኑንና የባሕርይ ልጅ መሆኑን ይህም የእምነት መሠረት መሆኑን ጭምር ነው::

በአጠቃላይ የወልድ ልጅነትና የሰው ልጆች የእግዚአብሐር ልጅነት የተለያየ *(የባሕርይና የጸጋ)* ስለሆነ *"ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ..አርጋለሁ"* *ዮሐ 20÷17* አለ:: በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የአብን ወላዲነት የወልድን ተወላዲነት ሰፍሮ እናገኛለን:: ሲጠቃለል የወልድ ልጅነት የባሕርይ ነው ያለመለየትና ያለ መከፈል ነው::

የአብ ወላዲነት

ስለ አብ ወላዲነት ደግሞ *"ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድሁህ"* መዝ *109(110) ÷3* ተብሏል:: በዚህ ጥቅስ ተናጋሪው አብ ነው: *"እግዚአብሔርም /አብ/ አለኝ አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድሁህ"* መዝ *2÷7* ተብሎ ስለ አብ ወላዲነት ተጽፎአል::

Scanned by CamScanner

የወልድ ተወላዲነት

"ተራሮች ገና ሳይመሠረቱ ከኮረብቶችም በፊት አኔ ተወለድሁ" ምሳ 8÷25 ተብሎ ስለ ወልድ ተወላዲነት ተነግሮአል:: በዚህ ጥቅስ ተናጋሪው ወልድ ነው:: ስለ ልደቱም ዘላለማዊነት ደግሞ *"አወጣጡ (አወላለዱ) ከቀድም ጀምሮ ከዘላለም የሆነ"* ሚክ 5÷2 ተብሎ መወለዱ ከጊዜ በኋላ የሆነ ሳይሆን የባሕርይና ዘላለማዊ መሆኑ ተነገሯል::

የመንፈስ ቅዱስ ሠራጺነት

አስቀድሞ እንደተመለከትነው የመንፈስ ቅዱስ የአካሉ ግብር ከአብ ብቻ መውጣት *(መሥረጽ)* ነው:: አበው ሊቃውንት በመጽሐፍ ቅዱስ *"መውጣት"* በሚል የሰፈረውን የመንፈስ ቅዱስ ከአብ መውጣት የሚያመለክተው ቃል *"መሥረጽ"* ብለው እንደሰየሙት ኢይተናል::

ሠራጺ የሚለው ቃል ሠረጸ ከሚለው የግእዝ ቃል የወጣ ነው:: ትርጉሙ ወጣ፣ በቀለ፣ተገኘ፣ እቆጠቆጠ ማለት ነው:: መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ ወጣ *(ሠረጸ)* ሲባል የባሕርይ ጸአት ነው:: ማለትም ያለመከፈል፣ ያለመለየት *(ያለተከፍሎ ያለተመትሮ)* እንዲሁም ያለመቀዳደምና ያለመከተል ነው:: መንፈስ ቅዱስ ከአብ ሠረጸ ሲባል ከአብና ከወልድ ለዓይን ጥቅሻ ያከል እንኳ ሳይቀድምና ሳይዘገይ ነው::

ከአብና ከወልድም ጋር እኩል ክብር ያለው ነው:: መጽሐፍ ስለ መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ ሠራጺነት ሲናገር *"ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ"* ዮሐ 15÷26 ብሎታል::

መሥረጹ በምሳሌ

ሊቃውንት የወልድን ከአብ መወለድ ከፀሐይ በሚወጣ ብርሃን እንደመሰሉት ሁሉ የመንፈስ ቅዱስን ከአብ መሥረጽ ደግሞ ከፀሐይ በሚወጣ ሙቀት መስለውታል:: ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ በፀሐይ ሙቀት ተመስሏል ማለት ነው::

Scanned by CamScanner

በፀሐይ፣ በብርሃኑ እና በሙቀቱ መካከል መለየትና መከፈል መቅደምና መከተል የለበትም። በአካላተ ሥላሴና በስማቸውም መካከል መለየትና መከፈል መቅደምና መከተል የለም።

የመንፈስ ቅዱስ ሠራጺነት ከአብ ብቻ ወይስ ከወልድም?

አርየንታል አብያተ-ክርስቲያናት *(ኢትዮጵያ፣ ግብፅ፣ ሶርያ፣ አርመንያ፣ ሕንድና ኤርትራ)* መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ መሥረጹን ይቀበላሉ። በቁስጥንጥያ የተጨመረውን አንቀጽ ይቀበላሉ። አንቀጹም ***"ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማኅየዊ ዘሠረጸ እምአብ ንሰግድ ሎቱ ወንሰብሖ ምሰለ አብ ወወልድ ዘነበበ በነቢያት"*** የሚል ነው። አንቀጹ ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ላይ ያላትን አቋም በግልጽ ያስረዳል።

ነገር ግን ከዚህ በተቃራኒ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስን ከወልድም የሠረጸ እንደሆነ ታምናለች። በአሥራ አንደኛው ምዕተ ዓመት (በ1048 ዓ.ም) በጸሎተ ሃይማኖት ላይ *Filioque* የሚል ቃል ጨምራለች። ቃሉ የላቲን ሲሆን ትርጉሙ ***"ከወልድም የሠረጸ"*** ማለት ነው። በእርግጥ መንፈስ ቅዱስ ከወልድም ሠረጸ የሚለው አመለካከት ቀደም ብሎ በስድስተኛው ምዕተ ዓመት በአስፖኝ ቤተ ክርስቲያን የተንጸባረቀ ነበር። ቤተ ክርስቲያኗ በአርዮሳውያን ላይ ከነበራት የመረረ ጥላቻ የተነሣ ወልድም ከአብ አያንስም ለማለት መንፈስ ቅዱስን አሥርጾታል ብላለች። መንፈስ ቅዱስ ከወልድም ሠርጿል የሚሉ ወገኖች *በዮሐ 15÷26* ላይ መንፈስ ቅዱስ ከወልድም መሥረጹ ያልተገለጠው ለትሕትና ነው ይላሉ። ነገር ግን ለትሕትና ቢሆን ኖሮ በጥቅሱ ላይ ወልድ *"እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላቸሁ"* ብሎ ፈናዊነቱን *(ላኪነቱን)* ባልተናገረም ነበር።

በተጨማሪም ጥቅሱን መንፈስ ቅዱስ ከወልድም ለመሥረጹ እንደማስረጃ አድርጎ ማቅረብ በሠራጺነትና በተፈናዊነት መካከል ያለውን ልዩነት ጠንቅቆ ካለመረዳት የሚመጣ በመሆኑ ሠራጺነትንና ተፈናዊነት ምን እንደሆኑ እንመልከት።

Scanned by CamScanner

ሠራጺነቱና ተፈናዊነቱ

ጌታችን መንፈስ ቅዱስን እንደሚልከ በተለያየ ሥፍራ ተናግሯል *ዮሐ15÷ 26፣ ዮሐ 16÷27፣ ሉቃ 24÷49* ተመልከት:: አንዳንድ ሰዎች በነዚህ ጥቅሶች ላይ *"መላክ"* ተብሎ የተገለጸውን *"መሥረጽ"* በሚል ተረድተውታል:: ነገር ግን በሠራጺነት እና በተፈናዊነት *(በመላክ)* መካከል ሰፊ ልዩነት አለ::ለዚህም ምክንያቱ ጌታ ብቻ መንፈስ ቅዱስን የሚልከ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስም ወልድን ልኳልና ነው:: *"ጌታ አግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል"* ኢሳ *48÷16* እንዲል:: ሌላው ነጥብ በሠራጺነቱና በተፈናዊነቱ መካከል ያለው ልዩነት *" ሠራጺነቱ"* ዘላለማዊ ባሕርይው ሲሆን *"ተፈናዊነቱ (መላኩ)"* ግን ጊዜያዊ ማለትም በበዓለ ሃምሳ በሐዋርያት ላይ ሲወርድ ያለውን ሁኔታና ወቅት ብቻ የሚያመለክት በመሆኑ ነው::

መንፈስ ቅዱስ ከወልድም ሠረጸ የሚሉ ወገኖች ሌላው እንደ ማስረጃ የሚያነሡት ጌታ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር *"ለኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋል"* ዮሐ *16÷14* ያለውን ቃል መነሻ በማድረግ ነው:: ነገር ግን ኃይለ ቃሉ የመንፈስ ቅዱስን ከወልድ መሥረጽ የሚያሳይ አይደለም:: ምንም ቢሆን *"ወሰዶ"* የሚለው ቃል *"ሠርጸ"* በሚል ሊተረጐም አይችልም:: አማናዊ ትርጉሙ ግን ወስዶ ሲል ከእኔ ቃልነት ወስዶ ይነግራችኋል ማለት ነው:: ምክንያቱም አብና መንፈስ ቅዱስ የሚናገሩት በወልድ ቃልነት መሆኑ የታወቀ ነው:: ሌላው እንደ ማስረጃ የሚያነሱት *"የልጁ መንፈስ"ገላ 4÷6:: "የክርስቶስ መንፈስ" ሮሜ 8÷9* [32] እና *"የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ" ፊሊ 1÷19* ተብሎ መነገሩን ነው::

እነዚህም ጥቅሶች ቢሆኑ መንፈስ ቅዱስ ከወልድም መሥረጹን የሚያሳዩ ሳይሆኑ መንፈስ ቅዱስ የወልድ ሕይወት መሆኑን ነው:: አለበለዚያማ መንፈስ ቅዱስ የጥበብ የማስተዋል የአውቀትና የፍቅር መንፈስ (ኢሳ *11÷2*) ስለተባለ መንፈስ ቅዱስ ከነዚህም ሠረጸ ልንል ነው? አይደለም::

---

32. መንፈስ ቅዱስ *"የአግዚአብሔር መንፈስ"* እና *"የክርስቶስ መንፈስ"* ተብሎ መጠራቱ *(ተካከሎ መጠራቱ)* ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ መሆኑን ይመለከራል *ሮሜ 8÷9::*

Scanned by CamScanner

መንፈስ ቅዱስ *"የማስተዋል መንፈስ"* ስለተባለ ከማስተዋል ወጣ ወይም ሠረጸ እንደማይባል ሁሉ *"የከርስቶስም መንፈስ"* ስለተባለም ከወልድ ወጣ ወይም ሠረጸ አያሰኝም።

አቡነ ሺኖዳም የመንፈስ ቅዱስን ከአብ ብቻ መሥረጽ ሲናገሩ ወልድ የእግዚአብሔር ጥበብ ከሆነና መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ሕይወት *(ማኅየዊ)* ከሆነ እንዴት ሕይወት ከጥበብ ሊወጣ ወይም ሊሠርጽ ይችላል? በማለት ይጠይቃሉ።

ቅዱስ ቄርሎስም መንፈስ ቅዱስ እንደ ምንጭ ከአብ የሚሠርጽ ሲሆን ነገር ግን ወልድ ደግሞ ወደ ፍጥረት ልኮታል ብሏል።

የአካል ሦስትነት

የሥላሴ ሦስትነት ከሚገለጥባቸው ነገሮች አንዱ አካል ነው። በአካል ሥላሴ ሦስት ናቸውና። ***"አንዘ ይሜለሱ በአካላት ወይትዋሐዱ በመለኮት"*** [One Ousia and Three Hypostases] ተብሎ በአካል ሦስት በመለኮት አንድ መሆናቸው ተገልጿል። ሰባልዮስ ግን ከመጽሐፍ የሌለ የኑፋቄ ሐሳብ ከራሱ አመንጭቶ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ አካል አንድ ገጽ ናቸው በማለት ሳተ። ቤተ ክርስቲያን በበኩሏ ሰባልዮስን በመቃወም ሦስት ገጽ አንድ ባሕርይ፣ ሦስት አካል አንድ አምላክ ሦስት ስሞች አንድ እግዚአብሔር እያለች ሥላሴ በገጽ በስምና በአካል ሦስት እንደሆኑ ታምናለች ትመሰክራለች።

አካል ምንድነው?

የሥላሴን የአካል ሦስትነት ለመረዳት *"አካል"* ምን እንደሆነ መረዳት ተቀዳሚ ነገር ነው። አካል ማለት ሰውነት ወይም ሥጋ ማለት አይደለም። ምክንያቱም አብና መንፈስ ቅዱስ ሥጋ ለብሰው ሰው አልሆኑምና። ስለሆነም አካል ባልን ጊዜ ቅርፅ ቁመት አኗኗር ማለታችን ነው። ከዚሁ ጋር ስለ አካል ስንነጋገር መዘንጋት የሌለብን ነገር አለ ይኸውም አካል በሁለት እንደሚከፈል ነው፣ የሚታይና የማይታይ በሚል።- *ቆላ 1÷15-16*

Scanned by CamScanner

ከዚህ አንጻር የሥላሴ አካላት ምድቡ ከማይታይ እንደሆነ ግልጽ ነገር ነው። የሥላሴ አካላት በየአቋማቸው፣ በየመልካቸውና በየስማቸው ጸንተው የሚኖሩ ናቸው። ማለትም አብ ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም መልክና ፍጹም አካል አለው። ለወልድም ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም መልክና ፍጹም አካል አለው። ለመንፈስ ቅዱስም ፍጹም ገጽ፣ ፍጹም መልክና ፍጹም አካል አለው። ስለዚህ በአካል ሦስት ተባለ። እነዚህ ሦስት አካላት ሳይለወጡና ሳይለዋወጡ፣ ሳይቀየሩና ሳይዋዋጡ በየራሳቸው በየአካላቸው ለዘላለም ጸንተው የሚኖሩ ናቸው።

እግዚአብሔር አካላዊነቱን ለመግለጥ በመጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ቦታዎች በሰው ያሉ የአካል ከፍሎች እንዳሉት ሆኖ ተገልጧል። ሰውም በፈጣሪ አርአያና አምሳል ተፈጠረ መባሉ ቅሉ ለዚሁ ነው። የተወሰኑት ለአብነት ያህል የሚከተሉት ናቸው። መጽሐፍ ስለ እግዚአብሔር **ገጽ** (ፊት)ና መልክ ሲናገር *"ከፊትህስ ወዴት ኣሸሻለሁ?"* ይላል *መዝ 138÷7፣ማቴ 10÷32፣ ፊሊ 2÷6* ስለ **ቅንድቦቹም** *"ቅንድቦቹም የሰው ልጆችን ይመረምራሉ"* መዝ *10÷4* ተባለ። ስለ ዓይኖቹና **ጆሮዎቹ** *"የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደ ጻድቃን ጆሮዎቹም ወደ ጩኸታቸው ነው"* ተባለ *መዝ 33÷15፣ መዝ 10÷4፣ ኢሳ 1÷15።* ስለ **እጆቹ** *"እጆችህ ሠሩኝ አበጃጁኝም"* እንዲል *መዝ 118÷73፣ መዝ 18÷1፣መዝ 88÷13* ተመልከት። ስለ **ጣቶቹ** *"በእግዚአብሔር ጣት የተፃፈባቸውን ከድንጋይ የሆኑ ሁለቱን የምስክር ፅላቶች ሰጠው"* ዘጸ *31÷18* አለ።ስለ **ጠጉሩ** *"የራሱም ጠጉር እንደ ጥሩ ጥጥ ነበር"* ዳን *7÷9* ተብሏል። ስለ **ራሱም** *"ራሱ ምዝምዝ ወርቅ ነው"* የሚል አለ *መኃ.5÷11* ስለ **አፍንጫው** *"እግዚአብሔርም መልካሙን መዓዛ አሸተተ"* ተባለ *ዘፍ 8÷21።* ስለ **ወገቡ** *"የወገቡም መታጠቂያ ጽድቅ፣ የጎኑም መቀነት ታማኝነት ይሆናል"* ይላል *ኢሳ 11÷5።* ስለ **እግሮቹ** *"ወደ እግሩ መረገጫ ስገዱ"* ተባለ *መዝ 98÷5፣ ማቴ5÷35፣ ዘካ 14÷4።* ስለ **አፉ** *"ከአለላፉት ወርቅና ብር ይልቅ የአፍህ ሕግ ይሻለኛል"* ተባለ።- *መዝ 118÷72* [33]

33. መጽሐፈ ምሥጢር ገጽ 34.

Scanned by CamScanner

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት እግዚአብሔር በሰው አካል ያሉ ብሎቶች እንዳሉት ሆኖ መገለጡ ሰው በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል መፈጠሩን ከማመልከታቸው ሌላ የእግዚአብሔርን አካላዊነት የሚያሳውቁ ናቸው::

የአካል ሦስትነት በመጽሐፍ ቅዱስ

መጽሐፍ ቅዱስ የአካላተ ሥላሴን ሦስትነት በተለያየ መልኩ ተናግሮታል:: የአካልን ሦስትነት ከሚያመለክቱ ጥቅሶች ጥቂቶቹን በዚህ ክፍል እንመለከታለን:: በኡሪት እግዚአብሔር በሦስት ሰዎች አምሳል መገለጡ ተጽፎ ይገኛል፤ *ዘፍ18÷1-8::*

ለአብርሃም የተገለጡት ሦስት ሰዎች ሥላሴ መሆናቸውን በሚያስረዳ ሁኔታ ከላይ ሦስት ሰዎች ካለ በኋላ በምዕራፉ መጨረሻ "*እግዚአብሔርም ከአብርሃም ጋር ንግግሩን በጨረሰ ጊዜ ሄደ አብርሃምም ወደ ሰፍራው ተመለሰ* " *ዘፍ18÷33* የሚለው አባባል ለአብርሃም በሦስት ሰዎች አምሳል የተገለጠለት እግዚአብሔር መሆኑን ያሳያል:: ቅዱስ አውግስጢንም ለአብርሃም የተገለጡለት ሦስቱ ሰዎች ሥላሴ መሆናቸውን ተናግሯል::[On Trinity P 47]በሌላ መልኩ ሦስትነትን በሚያሳይ ሁኔታ አንድን ቃል ሦስት ጊዜ ተደጋግሞ ሲነገር እናገኛለን:: ለምሳሌ " *አንተ ፊቴን አሹት ባልህ ጊዜ፡-አቤቱ ፊትህን አሻለሁ ልቤ አንተን አለ ፊትህን ከአኔ አትሰውር* " መዝ *26÷9* ይላል:: በዚህ ጥቅስ ላይ ሦስት ጊዜ *"ፊት"* የሚለው ተጠቅሷል:: ይኸውም የገጽና የአካል ሦስትነትን ያመለክታል::

መቼም መጻሕፍት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ነው የተጻፉት ብሎ የሚያምን ሰው ሦስት ጊዜ ፊት ተብሎ የተጠቀሰው በአጋጣሚ ነው ብሎ አያስብም:: ቤተ ክርስቲያንም ይህ ጥቅስ የአካልና የገጽን ሦስትነት የሚያመለክት እንደሆነ ታምናለች:: በዚህ መሠረት ***"ፊትህን"*** ተብሎ በቅድሚያ የተጠቀሰው አብን ሲያመለክት ነው:: ***"ፊትህን አሻለሁ"***የሚለው ደግሞ ወልድን ያመለክታል:: ***"ፊትህን ከአኔ አትሰውር"*** የሚለው ደ፡ግሞ መንፈስ ቅዱስን ያሳያል::

Scanned by CamScanner

ዳግመኛም አንድን ነገር ሦስት ጊዜ መናገር የሥላሴን ምሥጢር አመልካች በመሆኑ በመዝሙር መጽሐፍ "የእግዚአብሐር ቀኝ ኃይልን አደረገች:: የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አደረገችኝ:: የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች" መዝ 117÷16 ተብሎ ተጻፈ::

በተጨማሪም ሱራፌል "ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር" እያሉ ማመስገናቸው ሦስት ጊዜ ቅዱስ ማለታቸው የአካልን ሦስትነት የሚናገር ሲሆን ቃሉ አንድ ዓይነት መሆኑ አንድነታቸውን ይመሰከራልና ነው::

በዘመነ ሐዲስም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በሚሉ ሦስት ስሞች መገለጡ የአካልን ሦስትነት ያሳያል ማቴ 28÷19:: ምክንያቱም ስም ሊኖረው የሚችለው አካል ያለው ነገር ነውና ::

በጥምቀቱም የአካል ሦስትነት የተገለጠ በመሆኑ በዓለ ጥምቀት አስተርእዮ (መገለጥ) ተብሎ ይጠራል:: በዮርዳኖስ ጌታ በተለየ አካሉ በእደ ዮሐንስ ሲጠመቅ ታየ:: መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል ወርዶ በጌታ ራስ ላይ ተቀምጦ ታይቶአል:: አብ "የምወደው ልጄ" በማለቱ በተለየ አካሉ ህልው እንደሆነ ታወቀ::-ማቴ 3÷16-17፣2ጴጥ1÷17

በተጨማሪም "እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል" በማለቱ የአካል ሦስትነት ግልጥ ሆኖ ይታወቃል ኢሳ 48÷16:: "እግዚአብሔር" ሲል አብን፣ "መንፈሱ" ሲል መንፈስ ቅዱስን፣ "ልከውኛል" ሲል ራሱን ያመለክታል:: ዳግመኛም ስለ አባቱና ስለ ራሱ ሲናገር "የሁለት ሰው ምስክርነት እውነት ነው፣ እውነት እንደሆነ በሕጋችሁ ተጽፏል:: ስለ ራሴ የምመሰክር እኔ ነኝ የላከኝ አባቴ ስለ እኔ ይመሰክራል" ዮሐ 8÷17-19 በማለቱ በራሱና በአብ መካከል የአካል ልዩነት ያለ መሆኑን በግልጽ ተናግሮአል::በዚህም ሦስትነትን ከደው ኢየሱስ ብቻ የሚሉ የOnly Jesus አማኞች ይረታሉ::ምክንያቱም ራሱንና አብን በሁለት ሰዎች መስሎ ተናግሯልና ነው::

Scanned by CamScanner

በሌላም ቦታ መንፈስ ቅዱስን ጨምሮ ሲናገር *"እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ ሊድናኝ አርቡም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ፣ አርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል"* በማለት በአካል ሦስት፣ በግብር *(በመመሰከር)* አንድ መሆናቸውን ተናገረ::- *ዮሐ 15÷26*

በተጨማሪም ሥላሴ በገጽ ሦስት ናቸው:: ገጽ የሚባለው ልብስ የማይሸፍነው በላይ ያለው ከፍል ነው:: በቁሙ ፊት ይባላል:: ገጽ የአንድ ሰው መታወቂያ መለያ ወይም መገለጫው ነው:: ቅዱስ ዳዊት ስለ ሦስት ገጻት ሲናገር *"አቤቱ ፊቴን አሹት ባልህ ጊዜ አቤቱ ፊትህን አሻለሁ፣ ልቤ አንተን አለ ፊትህን ከእኔ አትሰውር"* መዝ *26÷8-9* በማለት ሥላሴ በገጽ ሦስት መሆናቸውን መሰከረ::

የመንፈስ ቅዱስ የባሕርይ አምላክነት

ቁጥሩ ከተረፈ አርዮሳውያን የሆነ የቁስጠንጥንያ ሊቀ ጳጳስ የነበረው መቅዶንዮስ የመንፈስ ቅዱስን የባሕርይ አምላክነት ከዶ ነበር:: መቅዶንዮስ መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ የሚያንስ፤ አካል የሌለው፣ ዝርው እና ፍጡር ነው ብሎ ያምን ነበር:: ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት አድርጋ መንፈስ ቅዱስን አካላዊ ከአብና ከወልድ ጋር የሚተካከል፣ እና ሁሉን የፈጠረ በማለት ታምናለች:: ***"ንአምን በመንፈስ ቅዱስ አግዚአ ማሕየዊ"*** ሕይወትን በሚሰጥ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን በማለት በመንፈስ ቅዱስ ላይ ያላትን እምነት ትመሰክራለች::

ፈጣሪነቱ

የመንፈስ ቅዱስ ፈጣሪነት ከጥንት ፍጥረት ጀምሮ የተገለጸ ነው:: *"የእግዚአብሔር መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር" ዘፍ 1÷2* የሚለው ኃይለ ቃል መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር በፍጥረት ሥራ አንድ መሆኑን ያሳያል:: ያማ ባይሆን ቃሉ ባልተነገረ ነበር:: ምክንያቱም እግዚአብሔር በፍጥረት ሥራው አማካሪ ወይም ረዳት እንደማያሻው ተጽፎአልና ነው::- *ኢሳ 40÷13*

Scanned by CamScanner

ጻድቁ ኢዮብም በግልጽ *"የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ፣ ሁሉንም የሚችል የአምላክ እስትንፋስ ሕይወትን ሰጠኝ"* ኢዮ 33÷4 በማለት የመንፈስ ቅዱስን የባሕርይ አምላክነት ተናገረ። ***"ሁሉንም የሚችል"*** በማለቱም መንፈስ ቅዱስ **ኤልሻዳይ** እንደሆነ መሰከረ። ሁሉን ቻይነት የአምላክ ብቻ ባሕርይ መሆኑ የታወቀ አይደለምን? አሁንም ፈጣሪነቱን በሚያሳይ አነጋገር *"በመንፈሱ ሰማያት ውበትን አገኙ..."* ኢዮ 26÷13 ተብሎአል። በዚህ ኃይለ ቃል *"መንፈሱ"* የተባለው መንፈስ ቅዱስ መሆኑ የታወቀ ነው። መጽሐፍ ብዙ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን *"መንፈስ"* ብቻ በሚል ይጠራዋል። ለምሳሌ በራእይ ስለ መንፈስ ቅዱስ በተደጋጋሚ የተገለጸው *"መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይሰማ"* ተብሎ ነው ራእ 2÷29፣3÷6፣13፣22 ተመልከት። በተጨማሪም በመዝሙር መጽሐፍ ስለ ፈጣሪነቱ *"መንፈስህን ትልካለህ ይፈጠራሉም"* ይላል መዝ 104÷30። *"በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ፣ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ"* መዝ 32÷6 የሚለውም ሌላኛው የመንፈስ ቅዱስን ፈጣሪነት አመልካች ጥቅስ ነው።

ማሕየዊነቱ

ምንም እንኳ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ **ማሕየውያን** *(ሕይወትን የሚሰጡ)* ቢሆኑም መንፈስ ቅዱስ በተለየ አካሉ በተለየ ግብሩ **ማሕየዊ** ይባላል። መንፈስ ቅዱስ ለአብና ለወልድ ለራሱም ሕይወት ነው። አንድም በነፍስ ሕያው ሆኖ ለተፈጠረ ፍጥረት ሁሉ ሕይወት ነው። በዚህ መሠረት መንፈስ ቅዱስ ማሕየዊ *(The Life-Giving)* ይባላል። መንፈስ ቅዱስ ሕይወት በመሆኑና ሕይወትን የሚሰጥ በመሆኑ አምላክነቱን እንረዳለን።

የመንፈስ ቅዱስን ማሕየዊነት ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ። ለምሳሌ በትንቢተ ሕዝቅኤል ብንመለከት የደረቁ አጥንቶችን ትንፋሽ *(መንፈስ ቅዱስ)* ገብቶባቸው እንደተነሡና በሕይወት መኖር እንደጀመሩ ተገልጸአል።- *ሕዝ 37÷1-10*

Scanned by CamScanner

በደረቁ አጥንቶች ገብቶ ሕይወትን የሰጣቸው ትንፋሽ *(ነፋስ)* መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ሲናገርም *"መንፈሴንም በውስጣችሁ አሳድራለሁ፣ አናንተም በሕይወት ትኖራላችሁ" ሕዝ 37÷14* በማለት የመንፈስ ቅዱስን ማሕየዊነት ተናገረ::

በራእየ ዮሐንስም ስለ ሁለቱ የተገደሉ ምስክሮች በተናገረበት ጊዜ *"ከሦስት ቀን ተኩልም በኋላ ከአግዚአብሔር የወጣ የሕይወት መንፈስ ገባባቸው በአግሮቻቸውም ቆሙ" ራዕ ፲፩÷፲፩* በማለት ከአብ የሠረጸ ቅዱስ መንፈስ ሲገባባቸው ሕይወት አግኝተው እንደ ቆሙ የተገለጸ ነው:: ለዚህ ነው ጌታችን *"ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው" ዮሐ 6÷63* በማለት የተናገረው:: ቅዱስ ጳውሎስም ማሕየዊነት አምላካዊ ባሕርይ እንደሆነ ሲያስረዳ *"ለሙታን ሕይወት በሚሰጥ የሌለውንም እንዳለ ኤድርጎ በሚጠራ ባመነበት በአምላክ ፊት የሁላችን አባት ነው"* በማለት ተናገረ *ሮሜ 4÷17፣ ፩ጢሞ 6÷13*:: እነዚህ ሁሉ ጥቅሶች የመንፈስ ቅዱስን ማሕየዊነትና አምላክነት ያስረዳሉ::

አምላክነቱ

እንደሚታወቀው አምላክ የራሱ የሆኑ ባሕርያት አሉት:: ሁሉን ቻይነት፣ ምሉዕ በኩለሄነት፣ ዘላለማዊነት፣ ሁሉን አዋቂነት ፈጣሪነት...ወዘተ ለአምላክ ብቻ የሚነገሩ ባሕርያት እንደሆኑ ከማንም የተሰወረ አይደለም:: መንፈስ ቅዱስ አምላክ በመሆኑ በቅዱሳት መጻሕፍት እነዚህ ባሕርያት ለእርሱ ተሰጥተው ተነግረው እናገኛለን:: በተመሳሳይ ለአብ ወይም ለወልድ የሚነገሩ ነገሮች ለመንፈስ ቅዱስ ተነግረው መገኘታቸው ከአብና ከወልድ ጋር አንድ እንደሆነና የባሕርይ አምላክ እንደሆነ ይመሰክራሉ::

ከአምላካዊ ባሕርያቱ ስንነሣ ምሉዕ በኩለሄነት *(በሁሉ ቦታ መገኘት)* ከባሕርያቱ አንዱ እንደሆነ እንረዳለን:: መንፈስ ቅዱስ በሁሉ የመላ ስለሆነ መዝሙረኛው *"ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ፣ አንተ በዚያ ነህ፤ ወደ ሲኦልም ብወርድ፣ በዚያ አለህ"* በማለት የመንፈስ ቅዱስን በሁሉ ቦታ መገኘትን ተናገረ::- *መዝ 139÷7-8*

Scanned by CamScanner

ሌላው አምላካዊ ባሕርይ ዘላለማዊነት ነው:: መንፈስ በባሕርይው ዘላለማዊ ስለሆነ *"በዘላለም መንፈስ"* ተብሎ ተጠርቷል::- *ዕብ 9÷14*

በተጨማሪም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የባሕርይ መተዋወቅ (መገናዘብ) አላቸው:: ይህ ማለት ፍጥረታት የማያውቁት ነገር ግን ሦስቱ አካላት ብቻ የሚተዋወቁት የባሕርይ መተዋወቅ ማለት ነው:: መጽሐፍ ስለዚህ መተዋወቅ ሲናገር *"ወልድን ማን አንደሆነ ከአብ በቀር የሚያውቅ የለም:: አብንም ማን አንደሆነ ከወልድ በቀር ወልድም ሊገልጥለት ከሚፈቅድ በቀር የሚያውቅ የለም"* ይላል *ሉቃ 10÷22::* ይህ እንዲህ ከሆነ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ የአብና የወልድ ሕይወታቸው በመሆኑ እና ተዋሕዶአቸው ያለ በመሆኑ አብና ወልድን የሚያውቅ እንደሆነ ጥርጥር የለውም:: ከዚህም እውቀቱ ተነሥተን አምላክነቱን ወይም አምላካዊ ባሕርይውን እንረዳለን:: ቅዱስ ጳውሎስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ባሕርያዊ እውቀት ሲናገር *"አንዲሁ ደግም ከአግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለአግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም"* *፩ቆሮ 2÷11* በማለት ገልጾታል::

ሁሉን አዋቂነት የመንፈስ ቅዱስ የባሕርይ ገንዘብ መሆኑን ቀደም ብሎ በተመለከትነው ከአብና ከወልድ ጋር ባለው የባሕርይ መተዋወቅ አይተናል:: ዳግመኛም አዋቂነቱ በፍጥረቱም ላይ ስለሆነ የሰዎችን የተደበቀ የልብ ሐሳብ ያውቃል ሐናንያ የተባለ ሰው መንፈስ ቅዱስን ለማታለል ሞከሮ እንደነበር ተጽፎአል:: *"ጴጥሮስም ሐናንያ ሆይ መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለምን ሞላ? ሳትሸጠው የአንተ አልነበረም?... አግዚአብሔርን አንጂ ሰውን አልዋሸህም"* አለው *ዮሐ 5÷3-6* በጥቅሱ ላይ *"መንፈስ ቅዱስን ታታልልና"* እና *"አግዚአብሔርን አንጂ ሰውን አልዋሸህም"* የሚሉት ሐረጎች መንፈስ ቅዱስን ማታለል እግዚአብሔርን መዋሸት መሆኑን ያስረዳል:: ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር በመሆኑ ነው::

መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ስለሆነ ለአብ ወይም ለወልድ የተነገሩ ነገሮች በብዛት ተነግረውለታል::

Scanned by CamScanner

ለምሳሌ ሰው የእግዚአሔር እና የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ ተጽፎአል። *"የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን?"* *1ቆሮ 3÷16፣ 1ቆሮ 6÷19።* መንፈስ የባሕርይ አምላክ ካልሆነ እንዴት በሰው ልብ ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር ይኖራል?

መጽሐፍ በጎ ሰጦታ ከየት እንደሆነ ሲናገር *"በጎ ሰጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፣ መለወጥ በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ"* *ያዕ 1÷17* ብሎ የስጦታ ምንጭ እግዚአብሔር መሆኑን ተናግሮአል። በዚህ አንጻር መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ስለሆነ ስጦታዎች ከመንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጡ ተገልጾ ይገኛሉ *1ቆሮ 12÷4-11።* ይህም መንፈስ ቅዱስ አምላክነት የባሕርይ ገንዘቡ እንደሆነ ማስረጃ ነው።

መንፈስ ቅዱስ ለፍጥረቱ ከአብና ከወልድ ስም ጋር በስሙ በጥምቀት አማካኝነት ልጅነት የሚሰጥ በመሆኑ *ማቴ 28÷19* እንዲሁም ከአብና ከወልድ ጋር የሚመሰከር በመሆኑ *1ዮሐ.መ 5÷7* በተጨማሪም በስሙ ከአብና ከወልድ ስም ጋር የምንባረክ ስለሆነ *2ቆሮ 13÷14* በአምላክነቱ ከአብና ከወልድ ጋር እናመልከዋለን። ሦስት ስም ሦስት አካል፤ አንድ መለኮት ብለን እናምነዋለን።

አካላዊነቱ

ጥንት መቅዶንዮስ ዛሬ ደግሞ ተረፈ አርዮሳውያን የይሖዋ ምስክሮች የመንፈስ ቅዱስን አካላዊነት በመካድ ዝርው፣ አንቀሳቃሽ ኃይል በማለት እንደነፉስ ይመለከቱታል። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ አካላዊ መሆኑን ታምናለች። ቅዱሳት መጻሕፍትም አካላዊነቱን ያረጋግጣሉ።

መንፈስ ቅዱስ በርግብና በእሳት አምሳል የታየ በመሆኑ አካላዊነቱን እንረዳለን *ማቴ 3÷16፣ ዮሐ 2÷1-4።* አንዳንዶች መንፈስ ቅዱስ *"ኃይል"* ነው እንጂ አካል የለውም ይላሉ።

Scanned by CamScanner

እኛ ደግሞ ኃይል ይናገራልን? በማለት እንጠይቃቸዋለን *"በእናንተ የሚናገር የአባታችሁ መንፈስ ነው"* ማቴ 10÷20። *"መንፈስ ቅዱስ በርናባስና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ"* ዮሐ 13÷2 ተብሏልና። በተጨማሪም ነፋስ ነው ይላሉ። ነፋስ ያስተምራል? ያሳስባል? ያጽናናልስ? ዮሐ 14÷26 ለሕዝቡና ለአብያተ ክርስቲያናትስ ነፋስ ሊናገር ይችላል? ዕብ 3÷7፣ ራእ 2÷7። ወይስ ደግሞ ኃይል ወይም ነፋስ መቀባትና መላክ ይችላል ሊሳ 61÷1-2 ወይም ደግሞ ነፋስ የርግብ ቅርጽ መንሣት ይችላል? ሉቃ 3÷22 በማለት እንጠይቃቸዋለን።

እኛ ግን እነዚህ ሁሉ ነገሮች አካል በሌለው በኃይል ወይም በነፋስ ሊሠሩ እንደማይችሉ እናውቃለን። ስለሆነም መንፈስ ቅዱስ በመናገሩ፣ በማስተማሩ ሰዎችን በማጽናናቱና በማሳሰቡ እንዲሁም በርግብ መልክ በመገለጡ ቤተ ክርስቲያን አካላዊ እንደሆነ ታምናለች። *"ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ አግዚአ ማሕየዊ ዘሠረጸ አምአብ፤ ንሰግድ ሎቱ ወንሰብሖ ምስለ አብ ወወልድ ዘነበበ በነቢያት።"*

የኩነት ሦስትነት

ምሥጢረ ሥላሴን ለመረዳት የሥላሴን ኩነት መረዳት የማዕዘን ድንጋይ ነው። ምክንያቱም የኩነት ምሥጢር ተዋሕዶተ ሥላሴ የሚታወቅበት ወይም የሥላሴ አንድነት የሚታወቅበት፣ የመገናዘብ ምሥጢር ያለበት እና ተጋብኦ በተከፍሎ፣ ወተከፍሎ በተጋብኦ ማለት አንድነት ሳለ መለየት መለየት ሳለ አንድነት ያለበት ትምህርት በመሆኑ ነው። እነዚህን ነገሮች በዝርዝር ለማየት ከመሞከራችን በፊት ኩነት ማለት ምን እንደሆነ እንመልከት።

ኩነት ምንድነው?

ኩነት ማለት *"መሆን"* ወይም *"መባል"* ማለት ነው። ለምሳሌ ከዊነ ልብ፣ ከዊነ ቃል፣ ከዊነ እስትንፋስ ሲል ልብ መሆን ወይም መባል፣ ቃል መሆን ወይም መባል፣ እስትንፋስ መሆን ወይም መባል ማለት ነው። ስለዚህ ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ ሦስቱ አካላተ ሥላሴ የሚጠሩበት የኩነታት ስም ነው ማለት ነው።

Scanned by CamScanner

ከዚህ የተነሣ ሥላሴ *(አብ፣ ወልድ መንፈስ ቅዱስ)* በኩነታት ሦስት ናቸው እንላለን:: የአብ ኩነት ልብነት ነው:: የወልድ ኩነት ቃልነት ነው:: የመንፈስ ቅዱስ ኩነት እስትንፋስነት ነው:: ዘርዘር ተደርጐ ሲታይ::

1. የአብ ኩነት ልብ *(ልብነት)* ሲሆን በራሱ ለራሱ ልቡና አእምሮ ነው:: ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ ልቡናቸው *(ማወቂያቸው)* ነው ከእርሱ ሌላ ልቡና የላቸውም::
2. የወልድ ኩነት ቃል *(ቃልነት)* ሲሆን በራሱ ለራሱ ቃል ነው:: ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው *(መናገሪያቸው)* ነው:: ከእርሱ ሌላ ቃል የላቸውም::
3. የመንፈስ ቅዱስ ኩነት እስትንፋስ *(ሕይወትነት)* ሲሆን በራሱ ለራሱ ሕይወት ነው:: ለአብና ለወልድ እስትንፋሳቸው *(ሕይወታቸው)* ነው:: ከእርሱ ሌላ ሕይወት የላቸውም::

ኩነታት በመጽሐፍ ቅዱስ

የሥላሴ ኩነት በመጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ስፍራ ተጠቅሷል:: አብ ልብ *(ማወቂያ ለውቃት)* እንደሆነ ወልድ ቃል *(መናገሪያ)* እንደሆነ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ *(ሕይወት)* እንደሆነ በማያሻማ መልኩ የተቀመጠ ትምህርት ነው::

የአብ ኩነት ልብነት ስለመሆኑ *"የእግዚአብሔር ምክር ግን ለዘላለም ይኖራል፣ የልቡም (የአብ) አሳብ ለልጅ ልጅ ነው"* *መዝ 32(33)÷11* ይላል:: በድጋሚ በመዝሙር መጽሐፍ *"ልቤ (አብ) መልካም ነገርን አፈለቀ"* ተብሎ የአብ ኩነት ተገልጿል *መዝ 44÷1::* እዚህ ላይ ተናጋሪው አብ ነው የወልድን ከእርሱ በቃልነት ከዊን መውጣት ሲናገር ነው። አሁንም ከመዝሙር መጽሐፍ ሳንወጣ ወልድ ተናጋሪ ሆኖ ስለ አብ ኩነት ሲናገር እናገኘዋለን:: *"ሁሉ ጊዜ እግዚአብሔርን በፊቴ አየዋለሁ በቀኜ ነውና አልታወክም:: ስለዚህ ልቤን (አብን) ደስ አለው"::- መዝ 15÷8-9*

Scanned by CamScanner

ይህ ቃል ለጊዜው ለዳዊት የተነገረ ቢሆንም ፍጻሜው ግን ለክርስቶስ ነው። ለክርስቶስ የተነገረ መሆኑን ለመረዳት የሐ.ሥራ 2÷22-36 መመልከት ጠቃሚ ነው። እነዚህ ጥቅሶች የአብ ኩነት ልብነት መሆኑን ያሳያሉ።

የወልድ ኩነት ቃል ስለመሆኑ ደግሞ "በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ" መዝ 32(33) ÷6 ተብሎአል። በወንጌልም "ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ" ዮሐ 1÷14 በማለት ወልድ ቃል እንደተባለና በተለየ አካል የሰውን ሥጋ መልበሱን ተናገረ። ሐዋርያው "ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደተዘጋጁ..." ዕብ 11÷3 በማለት በኩነት ስሙ ጠርቶታል። በራእየ ዮሐንስም ቃል የወልድ የኩነት ስሙ መሆኑን ሲገልጽ "ስሙም የእግዚአብሔር ቃል ተብሏል" ራዕ 19÷13 ተብሎ ተጽፎአል። ይኸውም የኩነት ስም የተባለው ነው።

የመንፈስ ቅዱስ ኩነት እስትንፋስነት መሆኑን በተመለከተ ከቡር ዳዊት "በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፋ አስትንፋስ" መዝ 32(33)÷6 ብሎ ተናግሯል። ኢዮብም "እርሱ ልቡን ወደ ራሱ ቢመልስ፣ መንፈሱንና እስትንፋሱን ወደ ራሱ ቢመልስ፣ ሥጋ ለባሽ ሁሉ በአንድነት ይጠፋል" ኢዮ 34÷14 በማለት የመንፈስ ቅዱስን ከዊነ እስትንፋስነት ተናገረ።

በተጨማሪ - ወልድ የአብ ቃል ስለመሆኑ።- ራዕ 19÷13

- ወልድ የመንፈስ ቅዱስ ቃል ስለመሆኑ።- ዮሐ 16÷13፣14÷15
- መንፈስ ቅዱስ ለአብ እስትንፋስ ስለመሆኑ።- ኢሳ 48÷16
- መንፈስ ቅዱስ ለወልድ እስትንፋስ ስለመሆኑ ገላ4÷5፣ኢሳ59÷21 ተመልከት።

Scanned by CamScanner

ለኩነት የነፍስ ምሳሌነት

እስከ አሁን በተመለከትነው ኩነት ምን እንደሆነ እና በመጽሐፍ ቅዱስ እንዴት እንደተቀመጠ ኢይተናል፡፡ ይሁንና የሥላሴ ኩነት ነገር ሰፋ ያለና በደንብ ሊረዱት የተገባ ስለሆነ፣ ለመረዳት ያመች ዘንድ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ነፍስ ከኩነት ጋር ያላትን ተዛምዶ ወይም ምሳሌነት በዝርዝር ያስተማሩ በመሆኑ እርሱን መመልከቱ ኦስፈላጊ ነው፡፡

ለኩነታት ምሳሌነት ከነፍስ የተሻለ ማሳያ የሚኖር ኢይመስልም፡፡ ምናልባት ሌሎች ምሳሌዎች ቢኖሩ እንኳ እንደ ነፍስ ኩነትን ለማሳየት የተጠጋ ምሳሌ ኢይሆኑም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ሰው ሲፈጠር በሥላሴ አርኣያና አምሳል የተፈጠረ በመሆኑ ነው *ዘፍ 1÷26፡፡* ነገር ግን ነፍስ ለኩነተ ሥላሴ ምሳሌ ናት ሲባል ምሳሌ ዘየሐፅፅ መሆኑን ልብ ማለት ይገባል፡፡ ምሳሌነቷን ስንመለከት፡-

የስም ተመሳሳይነት፡- የነፍስ ኩነታት *(ጠባያዓት)* ልብ ቃል እስትንፋስ ይባላሉ፡፡ የሥላሴም ኩነታት ልብ፣ ቃል እስትንፋስ ተብለው ይጠራሉ፡፡

ነፍስ በአካሏ አንድ ስትሆን በኩነቷ ግን ሦስት ናት፡፡ በዚህም ለሥላሴ አንድነት እና ሦስትነት ምሳሌ ትሆናለች፡፡

የነፍስ ኩነታት *(ልብ ቃል ኦስትንፋስ)* ህልውናቸው ቅደም ተከተል የሌለበት ነው፡፡ ለሥላሴም ኩነት ቃል እና እስትንፋስ ከአብ ሲወጡ ያለ ቅደም ተከተል ነው፡፡ በዚህ ምክንያት *"አብቲ ቅድምናሆሙ ለሥላሴ"* የሥላሴ ቅድምና አንዲት ናት ተብሎአል፡፡

የቃልና የእስትንፋስ ከልብ መገኘት ያለ መለየትና ያለ መከፈል ነው፡፡ ይህ በነፍስም በሥላሴም ኩነት ተመሳሳይ ነው፡፡ ሊቃውንት የነፍስን ኩነት በጥልቀት የተረዱ ስለሆነ ለሥላሴ ኩነታት ባየነው መልኩ ምሳሌ አድርገው አቅርበውታል፡፡ ነገር ግን ምሳሌነቱ ፍጹም ምሳሌ እንዳልሆነ የተጠቆመ ነው፡፡ *ነፍስ ለካሏ ለንድ መሆኑ ለና ለለመገናዘቧ ምሳሌ ዘየሐፅፅ ያሰኛታል፡፡* ምክንያቱም ሥላሴ በለካል ሦስት የሆኑና መገናዘብ ያላቸው በመሆኑ ነው፡፡

Scanned by CamScanner

በኩነታት መገናዘብ

የኩነታት ነገር መገናዘብ ያለበት ነው። መገናዘብ ሲባል አንድነትን መዋሐድን *(ተዋሕዶን)* ገንዘብ ማድረግን *(የራሰ ማድረግን)* ያመለክታል። ሦስቱ አካላተ ሥላሴም በሕልውና ይገናዘባሉ። ሥላሴ መገናዘባቸው በኩነታቸው ማለትም በልብነት በቃልነትና በእስትንፋስነት ነው። የኩነታት መገናዘብ የሥላሴን ተዋሕዶ *(አንድነት)* የሚያሳይ በመሆኑ ጠንቅቆ መረዳት ያሻል። ሥላሴ በኩነታት ሲገናዘቡ መለያየት የለባቸውም። ይህ በምሳሌ ሲታይ ቃል ከልብ ሲገኝ ወይም እስትንፋስ ከልብ ሲወጣ ያለመለየት እና ያለመከፈል እንደሆነው ሁሉ ማለት ነው። በተጨማሪም መገናዘባቸው ያለመለወጥና መፋለስ ነው። ይኸውም ልብ ቃል ወይም እስትንፋስ ወደ መሆን፣ ቃልም ልብ ወይም እስትንፋስ ወደ መሆን፣ እስትንፋስም፣ ልብ ወይም ቃል ወደ መሆን አይለወጥም አይፋለስም። በዚህ ይለያያሉና *(በመግቢያችን ላይ አንድነት ሳለበት መለየት ያለበት ነው ያልነው ይህንን ልዩነት ነው)*

የአብ ኩነት ልብነት ነው ሲባል እውቀት ወይም ማወቂያ የመሆን ከዋኔን፣ ቃልነት ሲባል መናገሪያ የመሆን ከዋኔን፣ እስትንፋስነት ሲባልም ሕይወት የመሆን ከዋኔን ያሳያል ያሰማል።

ሥላሴ በኩነታት ይገናዘባሉ ብለናል። ለአብ፣ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለው መገናዘብ *(ተዋሕዶ)* ልባቸው በመሆን ነው እንጂ አካላቸው በመሆን አይደለም። ምክንያቱም ወልድና መንፈስ ቅዱስ ልባቸው አብ ነው። ሌላ ልብ የላቸውም። በዚህ አንድ ይሆናሉ ይገናዘባሉ። አካልን በተመለከተ ግን ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ የተለየ የየራሳቸው አካል አላቸው። ለወልድም ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለው መገናዘብ ቃላቸው በመሆን ነው እንጂ አካላቸው በመሆን አይደለም። ለእነሱም በየራሳቸው አካል አላቸውና። መንፈስ ቅዱስም ከአብና ከወልድ ጋር ያለው መገናዘብ *(አንድነት)* ሕይወታቸው በመሆን ነው እንጂ አካላቸው በመሆን አይደለም።

Scanned by CamScanner

አንድነታቸው

ስለ ሥላሴ አንድነት *(ተዋሕዶ)* እንደ ሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል:: *"መቼም ብዙ አማልክትና ብዙ ጌቶች አሉ ነገር ግን በሰማይም ሆነ በምድርም ሆነ አማልክት የተባሉ ምንም ቢኖሩ፣ ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆነን አንድ አምላክ አብ አለን ነገር ሁሉ በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን" ፩ቆሮ 8÷5-6* :: ከጥቅሱ እንደምንረዳው አማልክት የተባሉ ጣዖታትና ጌቶች ብዙ ቢኖሩም እኛ ግን ከዚያ በተለየ አንድ አምላክ ብለን እንደምናመልክ ያሳያል:: ጥቅሱ ለምሳሌ የአብና የወልድን አንድነት ሲገልጽ አብን ሁሉ በእርሱ የሆነ ብሎታል:: በሌላ ቦታ ደግሞ ሁሉ በወልድ የሆነ እንደሆነ ተገልጿል::- *ዮሐ1÷3*

በተጨማሪም ከላይ በጥቅሱ እንደተመለከተው፣ ሁሉ *(እኛ)* ለአብ እንደሆንን ተገልጿል:: አብሮም ለወልድም እንደሆንን ተገልጿል *ቆላ 1÷16* ስለዚህ ከጥቅሱ በትንሹ አብና ወልድ በሁለት ነገሮች አንድነት እንዳላቸው ተገልጿል:: የመጀመሪያው *"ሁሉም በእነርሱ በመሆኑ"* አንድ ናቸው:: ሁለተኛ *"ሁሉም ለእነርሱ በመሆኑ"* አንድ ናቸው:: መንፈስ ቅዱስም ሕይወታቸው በመሆኑ አንድነት አለው *"መንፈስ ግን አንድ ነው"* እንዲል መጽሐፍ *፩ቆሮ 12÷4* ከዚህ የተነሣ ቤተ ክርስቲያን አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ብላ ታምናለች:: ጌታችን በወንጌል *"እኔና አብ አንድ ነን"* በማለት እንደተናገረ-*ዮሐ10÷30::*

ቅዱስ ጳውሎስ ከላይ እንደተመለከትነው የሥላሴ ሦስትነት አንድነታቸውን እንደ ማይከፍለው አንድነታቸው ሦስትነታቸውን እንደማይጠቀልለው ጠንቅቆ ስለተረዳ ልዩነትን *(ሦስትነት)* እና አንድነትን በሚያመለክት አነጋገር ተናግሯል *፩ቆሮ 8÷5-6* :: አባ ሕርያቆስ ይህን በግሩም ሁኔታ ሲያስረዳ *"አብርሃም ይስሐቅ ያዕቆብ በአካል ሦስት እንደሆኑ በባሕርይ ሦስት ብለን የምናምን አይደለም:: በአካል ሦስት ብንል በባሕርይ አንድ ብለን አናምለን እንጂ:: ከፍጥረት ሁሉ አስቀድሞ የነበረ አዳም በአካል አንድ*

Scanned by CamScanner

አንደሆነ በአካል አንድ ብለን የምናምን አይደለንም:: በባሕርይ አንድ ብለን በአካል ሦስት ብለን አናምናለን አንጂ" (ቅዳሴ ማርያም ገጽ 144) በማለት አንድ ስንል እንዴት እንደሆነ ሦስት ስንል እንዴት እንደሆነ መስከሯል:: በዚህ መንገድ ብቻ ነው ምስጢረ ሥላሴን ጠንቅቆ መረዳት የሚቻለው::

መጻሕፍት የሥላሴን ሦስትነት በስም በአካል በግብር እንዴት እንደሆነ እንደጠቀሱ ሁሉ አንድነትንም ጠቅሰውት ይገኛል:: "እስራኤል ሆይ ሰማ አምላካችን አግዚአብሔር አንድ አግዚአብሔር ነው" እንዲል ኦሪት ዘዳ 6÷4:: ነቢዩም "ለሁላችን አንድ አባት ያለን አይደለምን" ሚል 2÷10 በማለት የእግዚአብሔርን አንድነት አጠይቋል:: ስለዚህ መጽሐፍ አንድ አባት አንድ ወልድ አንድ መንፈስ በማለት የገለጸው አንድ አምላክ መሆኑን እንረዳ 1ቆሮ 8÷5-6፣ 1ቆሮ 12÷4:: በቁጥር ሕግ እንኳ 1x 1x1= 1 አይደለምን?

የእግዚአብሔርን አንድነት በተመለከተ አርጌንስ ሲናገር " አግዚአብሔር አንድ ብቻ ነው ምክንያቱም አንድ ሁለንታ ወይም አጽናፈ ዓለም (Universe) ፈጥሯልና " ብሏል በተጨማሪም "አምላክ አንድ ብቻ ካልሆነ አምላክ የለም " ሲል ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ ተናግሯል ::

አንድነታቸው በምንድነው?

የሥላሴ አንድነት በባሕርይ (ለባሕርዩ መነሻ ምክንያት የለውም የገዘ ራሱ ለራሱ ባሕርይ ነው)፣በህልውና (በኩነታት መገናዘብ አንዱ በአንዱ መኖር)፣ በመለኮት (ሊነገርና ሊመረመር ለማይችል ባሕርዩ መጠሪያ) [34] "መለኮትሰ ሊይትከሀል ይትበሃል ዘንተ የአከል ወዘንተ ይመሰል" መለኮት ግን አካሉ ይህን ያህላል መልኩ ይህን ይመስላል ሊሉት አይገባም እንዳለ ሕርያቆስ:: ከዚህም ሌላ በመንግሥት፣ በሥልጣን፣ ባገዛዝ (ምኩናን) አንድ ናቸው::

---

34. ከላይ እንደተገለጸው መለኮት የሚለው ስሙ ሊመረመር ለማይችል ባሕርይው መጠርያ ቢሆንም በቅዱሳት መጻሕፍት:-ብርሃን፣ሕይወት፣አገዛዝ፣ጌትነት፣ከብር፣ባሕርይ እና አምላክነት የሚል ትርጉም ያለው መሆኑ ተገልጾአል::

Scanned by CamScanner

በመሆኑም እግዚአብሔር በአንድነቱ ምንታዌ፡ በሦስትነቱ ርባኤ እንደሌለበት አውቀን ወይም ደግሞ አንድነቱ ሦስትነቱን እንደ ማይጨፈልቀው ሦስትነቱም አንድነቱን እንደ ማይከፋፍለው አውቀን ልዩ ሦስትነትን በአንድ መለኮትነት ወይም አምላክነት እንመን::

የሥላሴ ምሳሌ

ምንም እንኳን እግዚአብሔር ከባሕርየ ልዕልናው የተነሣ በምንም ዓይነት ምሳሌ ሊገለጽ ባይችልም ሊሳ *40÷18* ከማይነገር ፍቅሩና ከሚያስደንቅ ትሕትናው የተነሣ ደግሞ ራሱን በተለያዩ ነገሮች መስሎ ሲናገር እናገኛለን:: ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንም ይህን መነሻ በማድረግ የረቀቀውን የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት ልንረዳው በምንችልባቸው ልዩ ልዩ ምሳሌዎች መስለው አስተምረዋል:: እነዚህ ምሳሌዎች ፍጹም ስላልሆኑና እግዚአብሔርን በሙላት ሊገልጽ የሚችል ምሳሌ የሌለ በመሆኑ ምሳሌ ዘየሐፅፅ ወይም ጐዶሎ ምሳሌ እየተባሉ ይጠራሉ::

ከምሳሌዎቹም:-

1. **ነፍስ:-** ለሥላሴ የነፍስ ምሳሌት እንዴት እንደሆነ *"ለኩነት የነፍስ ምሳሌነት"* በሚለው ክፍል የተገለጠ በመሆኑ እዚህ ላይ መድገም አስፈላጊ አይደለም::

2. **ፀሐይ:-** ለፀሐይ ሦስት ነገሮች አሏት ከበብ፣ ብርሃንና ሙቀት፤ በከበቡ አብ፣ በብርሃኑ ወልድ፣ በሙቀቱ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል:: ከበቡ ብርሃንና ሙቀትን ያስገኛል እንጂ ብርሃን ከብነትና ሙቀትን ሙቀትም ከብነትና ብርሃንን አያስገኝም:: ሦስቱም ያለመለየትና ያለመቀዳደም በአንድነት ነበሩ::

የወልድ ብርሃንነት

የወልድ ብርሃንነት በተደጋጋሚ ተገልጾ ይገኛል *ዮሐ 1÷9፣ 12÷46፣ 8÷12::* ሐዋርያው ወልድ ከአብ ከብነት ስለወጣበት ብርሃንነቱ ሲናገር *"እርሱም የከብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ" ዕብ÷3* በማለት ገልጾታል::

Scanned by CamScanner

ይህ ኃይለ ቃል ታላቅ ምሥጢር የያዘ መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል። ወልድ ለአብ *"የከብሩ መንጸባረቅ"* ተብሎ መገለጡ ከአብ ከብነት የወጣ *(የተንጸባረቀ)* መሆኑን ከማስረዳቱ ሌላ በከብር የሚተካከለው እንደሆነ ያሳያል። በተጨማሪም *"የባሕርዩ ምሳሌ"* የሚለው ቃል ወልድ ከአብ ጋር ያለውን አንድነት ያሳያል። አለበለዚያ እግዚአብሔርን በባሕርይው ማን ሊመስለው ይችላልና ነው *"የባሕርዩ ምሳሌ"* የተባለው?

ሐዋርያው *"የከብሩ መንጸባረቅ"* ያለው አብ እና ነጸብራቁ ወልድ አንድ መሆናቸውን ሲናገር ነው። ምክንያቱም ብርሃንና ነጸብራቁን መለየት አይቻልምና ነው። ነጸብራቅ ብርሃን አከሎ ብርሃን መስሎ እንደሚወጣ የታወቀ ነውና። ስለዚህ ነጸብራቅን ማየት ብርሃንን ማየት ነው። ለዚህ ነው ጌታችን በወንጌል *"እኔን ያየ አብን አየ"* ዮሐ *14÷16* በማለት የተናገው። ይህን በማየቱ ወንጌላዊው *"ከአባቱ ዘንድ አንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን"* ዮሐ *1÷14* በማለት ተናገረ። ለዚህም ነው ቤተ ክርስቲያን ***"ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ"*** የምትለው። ነቢዩ ብርሃኑና ነጸብራቁ *(ጸዳሉ)* ልዩነት እንደሌላቸው ሲገልጽ *"ጸዳሉም አንደ ብርሃን ነው"* ብሏል።- *ዕንባ 3÷4*

የመንፈስ ቅዱስ ሙቀትነት

ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙቀትነት *"ከትኩሳቱም የሚሰወር የለም"* መዝ *18/19÷6* ተባለ። በሌላም ቦታ *"ፀሐይ ከትኩሳቱ ጋር ይወጣልና"* ተባለለት *ያዕ 1÷11፣ ኢሳ 40÷7።* አሁንም ነቢዩ ሲናገር *"እግዚአብሔር በፀሐይ ጮራ አንደ ደረቅ ትኩሳት...ሆኖ በማደርያዬ በፀጥታ ተቀምጬ አመለከታለሁ ብሎኛል"* ኢሳ *18÷4* ሲል ተናግሮአል። አሁንም በማያሻማ መልኩ *"የእግዚአብሔርም አስትንፋሰ አንደ ዲን ፈሳሽ ያቀልጠዋል"* ኢሳ *30÷33* በማለት የመንፈስ ቅዱስን ሙቀትነት ተናገረ። እነዚህ ጥቅሶች እግዚአብሔር በፀሐይ መመሰሉንና ትኩሳቱም መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ያስረዳሉ።

Scanned by CamScanner

3. እሳት፡- ሌላው የሥላሴ ምሳሌ እሳት ነው፡፡ እሳት አካሉ አንድ ሲሆን ሦስት ሁኔታዎች አሉት፡፡ እነርሱም ነበልባል፣ ብርሃንና ሙቀት ናቸው፡፡ በነበለባሉ አብ፣ በብርሃኑ ወልድ በሙቀቱ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል፡፡ ስለ እሳታዊ ባሕርይው *ዘዳ 3÷2-7፣ ዘዳ 9÷3፣ ሚል 3÷2-4 ዮሐ 2÷1-5* ተመልከት፡፡

4 ባሕር፡- ባሕር አካሉ አንድ ሲሆን ሦስት ነገሮች አሉት፡፡ ስፋት፣ ርጥበትና ማዕበል ናቸው፡፡ በስፋቱ አብ፣ በርጥበቱ ወልድ፣ በማዕበሉ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል- *መዝ 50÷1* እና ቁ 7 ኤር 7 ተመለከት፡፡

ምሥጢረ ሥላሴ በመጽሐፍ ቅዱስ

ተረፈ አርዮሳውያን የምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የሌለውና በ325 ዓ.ም በኒቅያ ጉባኤ በሠለስቱ ምዕት የተጀመረ *(የተደነገገ)* ነው በማለት ይናገራሉ *(በይሐዋ ምስክሮች የዘጋጀ በሥላሴ ማመን ይገባሃልን? የሚለው ብሮሹር ገጽ 7 ተመልከት፡፡)* ይህ በእርግጥ ያፈጠጠ ውሸት ነው፡፡ ምን አልባት ይህ ዓይነቱ እርግጠኛ የሚመስል አገላለጽና መረጃ የቀረበበት የሚመስል ንግግር የዋህንን ግር የሚያሰኝ ከመሆን ውጪ ነጭ ውሸት ነው፡፡

ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ አኳያ እንኳ ከሠለስቱ ምዕት በፊት በመጀመሪያዎቹ ሦስት መቶ ከፍለ ዘመን የነበሩ አበው እና ሊቃውንት በአሚነ ሥላሴ የጸኑ እንደነበሩ እንረዳለን ፡፡ ከእነዚህም መካከል ቅዱስ ቀሌምንጦስ ዘሮማ ፣ ቅዱስ አግናጥዮስ ፣ ቅዱስ ፖሊካርፐስ ፣ አርስታድ [*Aristide*] ፣ ሰማዕቱ ቅዱስ ዮስጢኖስ [*st. Justin*] ፣ አቴናጎራስ [*Athenagoras*] ፣ ቅዱስ ቴዎፍሎስ [*st. Theophilus of Antioch*] ፣ ሄሬኔዎስ ፣ ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ ፣ አርጌንስ ፣ ጠርጠሉስ ፣ ኖቫቲያን [*Novatian*] የመሰሉ ቅዱሳንና ሊቃውንት በሥላሴ አንድነትና ሦስትነት ያምኑ እንደነበር ትተዋቸው ያለፉዋቸው ጽሑፎቻቸውና ትምህርቶቻቸው አሁንም ያሉ ሕያው ምስክሮች ናቸው፡፡[35]

35. The Christian Orthodox Confession of Faith.p 55.

Scanned by CamScanner

የምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት በብሉይና በሐዲስ የተገለጠ መሠረተ እምነት (ዶግማ) ነው። በእርግጥ እስካሁን እንደተመለከትነው የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት የሚያስረዱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች ከሊቃውንት ትምህርት ጋር በማዛመድ የተመለከትን ቢሆንም በዚህ ከፍል ለብቻው ምሥጢረ ሥላሴን የሚያስረዱ ጥቅሶችን መመልከቱ ትምህርቱ ምን ያህል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐቅ እንደሆነ ለመረዳት የሚያግዝ ስለሆነ ጥቂቶቹን እንመልከት።

በኦሪት በጐላና በተረዳ መንገድ አንድነትና ሦስትነት አይገለጽ እንጂ ትምህርቱ ለተወሰኑ ደጋግ አበው የተገለጠ ነበር። ለምሳሌ በኦሪት ዘፍጥረት *"እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ባደረገ ቀን" ዘፍ 2÷4* ተብሎ የተገለጸው በዕብራይስጡ በኩር ጽሑፍ እግዚአብሔር የሚለው በነጠላ ቁጥር ሳይሆን በብዙ ቁጥር *"Elohim"* ተብሎ ነው የተጻፈው። ይህ ትምህርተ ሥላሴን የሚያመለክት በመሆኑ ነው በዚህ መልኩ እንዲጻፍ የሆነው። በተጨማሪም *"እግዚአብሔር አለ ሰውን በመልካችንና እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር" ዘፍ 1÷26* እና *"እነሆ አዳም መልካሙንና ክፉውን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ" ዘፍ 3÷22* ቡጨማሪም *"እግዚአብሔር አለ...ኑ እንውረድ እንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማ ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው" ዘፍ 11÷6-7* የሚሉት ጥቅሶች በብዙ ቁጥር ከመነገራቸው ሌላ ከሁለት አካል በላይ በሆኑ አካላት የተነገሩ መሆናቸውን ያስገነዝበናል።

ቅዱስ ባስልዮስ ታላቁ *"እግዚአብሔር አለ ሰውን በመልካችንና እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር" ዘፍ 1÷26* የሚለው ቃል "እግዚአብሔር ከራሱ ጋር መነጋገሩ ነው" የሚሉትን አይሁድ ነቅፎ ሲያስረዳ የትኛው አንጥረኛ ወይም አናጺ ወይስ ደግሞ ጫማ ሰፊ ነው ያለ ረዳት በዕቃዎቹና በንግዱ ፊት ብቻውን ሆኖ ለራሱ *"ሰይፍ እንሥራ" "ማረሻ አናብጅ"* ወይም *"ጫማ እንስፋ"* የሚለው?ሥራውን በጸጥታ አይሠራምን?በማለት ጥቅሱ ከአንድ በላይ ለሆኑ አካላት እንደተነገረ አስረዳ።

Scanned by CamScanner

በተጨማሪም ጥቅሱ የሚያመለክተው "እግዚአብሔር ከመላእክት ጋር መነጋገሩ ነው" የሚለውን የአይሁድ ልብ ወለድ ተቃውሞ ሲናገር "አንድን አካል(ወልድን) ላለመቀበል ብዙዎችን(መላእክትን) ተቀበሉ ልጁን ላለመቀበል አገልጋዮቹ መላእክትን በአማካሪነት ደረጃ ከፍ አደረጓቸው እንደ እኛ የተፈጠሩ መላእክትን በፍጥረታችን ተሳታፊ አደረጓቸው" በማለት ወቅሷቸዋል::

"በመልካችን እንደ ምሳሌያችን" ስለሚለው ቃልም ቅዱስ ባስልዮስ ሲናገር "በመልካችን ስለሚለው ቃል ምን ትመልሳለህ? አንዱ የእግዚአብሔር ሌላው ደግሞ የመላእክት መልክ ነው? ይልቁንም አብ እና ወልድ ፍጹም በመለኮታዊ ክብር አንድ ናቸው:: *"እርሱም የከብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ"ዕብ1÷3:: "እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ" ቆላ1÷15 :: "እኔና አብ አንድ ነን" ዮሐ 10÷13::* እንዲሁም *"እኔን ያየ አብን አይቶአልና" ዮሐ 14÷9:: ያለው አምላክ ነው ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር ያለው* በማለት ቅዱስ ባስልዮስ ታላቁ ተናግሮአል::[36]

ሌላኛው የምሥጢረ ሥላሴ አስረጅ ጥቅስ በኦሪት የተነገረው በዘፍጥረት *19÷25* ያለው ነው:: ጥቅሱ *"እግዚአብሔርም በሰዶምና በገሞራ ላይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሰማይ እሳትና ዲን አዘነበ"* የሚለው ነው:: በግልጽ እንደምንመለከተው *"እግዚአብሔር ከእግዚአብሔር ዘንድ እሳት አዘነበ"* ተብሎ መነገሩ ምሥጢረ ሥላሴን የሚያመለክት ከመሆን ባሻገር ምንድነው?

በተጨማሪም በትንቢተ ኢሳይያስ *"አንዱም ለአንዱ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚብሔር ምድር ሁሉ ክብሩ ተሞልታለች አለ ይጮህ ነበር"* ኢሳ *6÷3* ተብሎ የተነገረው ግልጽ የሆነ የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት የሚያመለክት ቃል ነው:: ለአባባላችን ማስረጃ እናቅርብ::

36. The Hexaemeron.

Scanned by CamScanner

አንደኛ በጥቅሱ ላይ "ጌታ" ተብሎ የተገለጸው ቃል በነጠላ ቁጥር ጌታ *(Adon)* ተብሎ ሳይሆን የተገለጸው በብዙ ቁጥር *"Adonai"* ተብሎ ነውና የተገለጸው ምሥጢረ ሥላሴን ያስረዳል::

ሁለተኛ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሚለው ቃል ሦስት ጊዜ መደጋገሙ ሦስትነትን ሲያመለክት ቃሉ አንድ ዓይነት መሆኑ አንድነትን ያሳያል::

ሦስትኛ ዝቅ ብሎ በተገለጸው አገላለጽ ለሥላሴ መነገሩን እንረዳለን:: ጥቅሱ የሚለው *"የጌታም ድምፅ ማንን ልልካለሁ ማንስ ይሄድልናል ሲል ሰማሁ"* ኢሳ *6÷8* የሚለው ነው:: ማንን እልካለሁ? እያለ በነጠላ ቁጥር መናገሩ *"ማንስ ይሄድልናል?"* ብሎ በብዙ ቁጥር መናገሩ አንድነትና ሦስትነትን የሚያመላክት አይደለምን? ቅዱስ ሥሉስ ማለትስ ከዚህ ሌላ ምንድነው?

አራተኛው ማስረጃ በሐዲስ ኪዳን ከላይ የሰፈረው ጥቅስ ሦስትነትን የሚያመለክት እንደሆነ መገለጹ ነው:: ኢሳይያስ በሱራፌል አንደበት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እየተባለ ሲመሰገን ከተመለከታቸው አንዱ ወልድ መሆኑን ወንጌላዊው ሲመሰክር *"ከብሩን ሰለ አየ ኢሳይያስ ይህን አለ ሰለ አርሱም (ኢየሱስ ክርስቶስ) ተናገረ"* ዮሐ *12÷41* በማለት ስለ ወልድ መነገሩን ገለጸ::

ዳግመኛ በሦስትነት ከተገለጸው አንዱ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነና ለኢሳይያስም የተናገረው እርሱ መሆኑን ሉቃስ ሲገልጽ *"መንፈስ ቅዱስ በነቢዩ በኢሳይያስ ለአባቶቻችን ወደዚህ ሕዝብ ሂድና መስማትስ ትሰማላችሁ አታስተውሱም...ሲል መልካም ተናገረ"* ዮሐ *28÷ 25-27፣* ኢሳ *6÷9-10* በማለት በሦስትነት ተገልጾ ለኢሳይያስ ከተናገረው አንዱ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ መሰከረ:: በተጨማሪም ይህ ጥቅስ የመንፈስ ቅዱስን እግዚአብሔርነት ያስረግጣል:: አብን *(አግዚአብሔርን)* የሚያመለክት መሆኑ ደግሞ በአይሁድ ትውፊት የተገለጸ ነው:: ስለዚህ ሱራፌል ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ ያመሰገኑት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን እነዚህ መረጃዎች ያሳያሉ::

Scanned by CamScanner

በመሆኑም ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ጥቅሱ ምሥጢረ ሥላሴን የሚናገር መሆኑን አረጋግጧል:: እንግዲህ ትምህርተ-ሥላሴን አምኖ ለመቀበል ይህ ጉልህ ማስረጃ ነው::

በዘመነ ሐዲስ ምሥጢረ ሥላሴ በጐላና በተረዳ መንገድ የተገለጠ ነው:: *"በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው" ማቴ 28÷19* በማለቱ ሦስቱ ስም ሦስትነትን የሚያመለክት ሲሆን *"ስም"* ተብሎ በአንድ መገለጡ አንድነትን ያሳያል:: በተጨማሪ በእነዚህ ስሞች ማለትም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በሚሉት ሦስት ስሞች አንድ ዓይነት ተግባር መፈጸሙ ማለት ምእመናን ተጠምቀው ልጅነትን ማግኘታቸው የአንድነትንና የሦስትነትን ምሥጢር ያሳያል:: ምክንያቱም በሰው *(በፍጡር)* ስም ጥምቀት አይፈጸምምና ነው *ፊቆሮ 1÷13::* ሌላው *"ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ ለርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ሰለ እኔ ይመሰክራል"* የሚለው ግልጽ የሦስትነት ማስረጃ ነው *ዮሐ 15÷26* በተጨማሪ ሐዋርያው *"የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም አንድነት ከሁላችሁ ጋር ይሁን"* በማለት ቡራኬ መስጠቱ ምእመናን በሦስቱ ስም አንድ በረከትን እንደሚቀበሉ ያሳያል:: ይህ የሐዋርያው ቡራኬ በኦሪት ከተጠቀሰው ቡራኬ ጋር ተመሳሳይ ነው:: *-ዘፍ 6÷24*

ታዲያ ትምህርተ-ሥላሴ ሠለስቱ ምዕት በጉባኤ ኒቅያ የፈጠሩት ነው ወይስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ?በእርግጥም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ነው::

Scanned by CamScanner